# የማርቆስ ወንጌል

የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወንጌል
ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ቅዱስ ማርቆስ እንደ ጻፈው።

---

## ምዕራፍ ፩

### ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ስብከት

(ማቴ. ፫፥፩-፲፪)

፩ የሕያው[፩] እግዚአብሔር ልጅ የጌታችን የኢየ
ሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ ይህ ነው። ፪ በነ
ቢያት[፪] እንደ ተጻፈ “እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ
የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ። ፫ የእ
ግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ፤ ጥርጊያውንም አስ
ተካክሉ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ የአዋጅ ነጋሪ
ድምፅ፤” ፬ ዮሐንስም በምድረ በዳ ያጠምቅ ነበር፤
ኀጢአትንም ለማስተስረይ የንስሓ ጥምቀትን ይሰ
ብክ ነበር። ፭ የይሁዳና የኢየሩሳሌምም ሰዎች ሁሉ
ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር፤ ኀጢአታቸውንም እየተና
ዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ሁሉንም ያጠምቃቸው ነበር።
፮ የዮሐንስም ልብሱ የግመል ጠጉር ነበር፤ ወገቡ
ንም በጠፍር መታጠቂያ ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም
አንበጣና የበረሃ ማር ነበር። ፯ እንዲህም እያለ ይሰ
ብክ ነበር፥ “ከእኔ ይልቅ የሚበረታ፥ ተጐንብሼ
የጫማዉን ማሰሪያ ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ
ይመጣል፤ ፰ እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ እርሱ
ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል።”

### ስለ ጌታችን ጥምቀት

(ማቴ. ፫፥፲፫--፬፥፲፩፤ ሉቃ. ፫፥፳፩-፳፪)

፱ ያንጊዜም ጌታችን ኢየሱስ ከገሊላ ናዝ
ሬት መጣ፤ ዮሐንስም በዮርዳኖስ ወንዝ አጠ
መቀው። ፲ ወዲያውም ከውኃዉ በወጣ ጊዜ፥
ሰማይ ሲከፈት፥ መንፈስ ቅዱስም እንደ ርግብ
ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት አየ። ፲፩ ከሰማ
ይም፥ “የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፤ በአንተም
ደስ ይለኛል” የሚል ድምፅ መጣ።
፲፪ ያንጊዜም መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ በዳ
አወጣው። ፲፫ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት በም
ድረ በዳ ተቀመጠ፤ ከሰይጣንም ይፈተን ነበር፤
ከአራዊትም ጋር ነበር፤ መላእክትም ያገለግ
ሉት ነበር።

### ጌታችን ማስተማር ስለ መጀመሩና ሐዋርያትን ስለ መምረጡ

(ማቴ. ፬፥፲፪-፳፪፤ ሉቃ. ፬፥፲፬-፲፭)

፲፬ ዮሐንስንም ከያዙት በኋላ ጌታችን ኢየሱስ
ወደ ገሊላ መጥቶ የእግዚአብሔርን የመንግሥት
ወንጌል ሰበከ። ፲፭ እንዲህም አለ፥ “ጊዜዉ
ደረሰ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና
ንስሓ ግቡ፤ በወንጌልም እመኑ።” ፲፮ በገሊላ
ባሕር አጠገብ ሲያልፍም ስምዖንንና ወንድሙ
እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ
አገኛቸው፤ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና። ፲፯ ጌታችን
ኢየሱስም፥ “ኑ ተከተሉኝ፤ ሰውንም የምታጠ
ምዱ አደርጋችኋለሁ” አላቸው። ፲፰ ያንጊዜም
መረባቸውን ትተው ተከተሉት። ፲፱ ከዚያም
ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስን ልጆች ያዕቆ
ብንና ወንድሙ ዮሐንስን በታንኳ ላይ መረባ
ቸውን ሲያበጁ አገኛቸው፤ እርሱም ከእነርሱ

---

፩ ግሪኩ “የሕያው ...” አይልም።

፪ አንዳንድ የግሪክ ዘርዕ “በኢሳይያስ” ይላል።

፩፥፪ ሚል. ፫፥፩። ፩፥፫ ኢሳ. ፵፥፫። ፩፥፮ ፪ነገ. ፩፥፰።

፩፥፲፩ ዘፍ. ፳፪፥፪፤ መዝ. ፪፥፯፤ ኢሳ. ፵፪፥፩፤ ማቴ. ፫፥፲፯፤ ፲፪፥፲፰፤ ማር. ፱፥፯፤ ሉቃ. ፫፥፳፪።

፩፥፲፭ ማቴ. ፫፥፪።

ጋር ነበር።፫ ፳ያንጊዜም ጠራቸው፤ አባታቸ
ውን ዘብዴዎስንም ከሙያተኞቹ ጋር በታንኳ
ውስጥ ትተው ተከትለውት ሄዱ።

### በምኵራብ ስለ ማስተማሩና ጋኔን የያዘውን ስለ መፈወሱ

(ሉቃ. ፬፥፴፩-፴፯)

፳፩ወደ ቅፍርናሆምም ሄዱ፤ ወዲያውም
በሰንበት ወደ ምኵራብ ገብቶ ያስተምራቸው
ጀመረ። ፳፪ትምህርቱንም አደነቁ፤ እንደ ጻፎ
ቻቸው ያይደለ እንደ በዓለ ሥልጣን ያስተም
ራቸው ነበርና። ፳፫በዚያም ጊዜ በምኵራባቸው
ውስጥ ክፉ ጋኔን ያደረበት ሰው ነበር። ፳፬እር
ሱም፥ "የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር
ምን አለን? ልታጠፋን መጥተሃልን? የእግዚአብ
ሔር ቅዱስ ሆይ፥ አንተ ማን እንደ ሆንህ ዐው
ቄሃለሁ" ብሎ ጮኸ። ፳፭ጌታችን ኢየሱስም፥
"ዝም በልና ከእርሱ ውጣ" ብሎ ገሠጸው።
፳፮ያ ክፉ ጋኔንም አፈራገጠውና በታላቅ ቃል
ጮኾ ከእርሱ ወጣ። ፳፯ሁሉም አደነቁ፤ እርስ
በርሳቸውም፥ "ይህ አዲስ ትምህርት ምንድን
ነው? ርኩሳን አጋንንትን ውጡ ብሎ ያዝዛቸ
ዋልና፤ እነርሱም ይታዘዙለታልና" ተባባሉ።
፳፰ዝናዉም በገሊላ አውራጃዎች ሁሉ ተሰማ።

### ስለ ጴጥሮስ አማት

(ማቴ. ፰፥፲፬-፲፯፤ ሉቃ. ፬፥፴፰-፵፯)

፳፱ወዲያውም ከምኵራብ ወጥቶ ከያዕቆብና
ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና ወደ እንድርያስ
ቤት ገባ። ፴የስምዖን አማትም በንዳድ ታማ
ነበር፤ ስለ እርስዋም ነገሩት። ፴፩ወደ እርስዋም
ቀርቦ እጅዋን ይዞ አስነሣት፤ ያንጊዜም ንዳ
ድዋ ተዋት፤ ተነሥታም አገለገለቻቸው።

### ብዙ በሽተኞችን ስለ ማዳኑ

፴፪ፀሐይ ገብቶ በመሸ ጊዜም፥ ድውያን
ንና አጋንንት ያደሩባቸውን ሁሉ ወደ እርሱ
አመጡ። ፴፫የከተማዪቱ ሰዎችም ሁሉ በደጅ
ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ፴፬በልዩ ልዩ ደዌ የታመ
ሙትን ብዙዎችን ፈወሳቸው፤ ብዙዎች አጋን
ንትንም አወጣ፤ እርሱም ክርስቶስ እንደ ሆነ
ዐውቀዋልና እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም።
፴፭በጥዋትም እጅግ ማልዶ ተነሣ፤ ወጥቶም
ወደ ምድረ በዳ ሄደ፤ በዚያም ጸለየ። ፴፮ስምዖ
ንና አብረውት የነበሩትም ተከተሉት። ፴፯ባገ
ኙትም ጊዜ፥ "ሁሉ ይፈልጉሃል" አሉት።
፴፰እርሱም፥ "ተነሡ፤ ወደ ሌሎች መንደሮ
ችም እንሂድ፤ በዚያ እሰብክ ዘንድ ስለዚህ
መጥቻለሁና" አላቸው። ፴፱በገሊላ ሁሉ በየ
ምኵራባቸው ተዘዋውሮ አስተማረ፤ አጋንንት
ንም ያወጣ ነበር።

### ለምጻሙን ስለ ማንጻቱ

(ማቴ. ፰፥፩-፬፤ ሉቃ. ፭፥፲፪-፲፯)

፵ለምጻም ሰውም ወደ እርሱ መጣ፤ ተንበ
ርክኮም፥ "አቤቱ፥ ከወደድህስ ልታነጻኝ ትች
ላለህ" ብሎ ለመነው። ፵፩ጌታችን ኢየሱስም
ራራለት፤ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፥ "እፈቅ
ዳለሁ ንጻ" አለው። ፵፪ይህንም በተናገረ ጊዜ
ለምጹ ፈጥኖ ለቀቀውና ነጻ። ፵፫መክሮም አሰና
በተው። ፵፬"ለማንም እንዳትናገር ዕወቅ፤ ነገር
ግን ሂድና ራስህን ለካህን አስመርምር፤ ምስክ
ርም ሊሆንባቸው ሙሴ እንዳዘዘ ስለ መንጻትህ
መባህን አቅርብ" አለው። ፵፭እርሱ ግን በወጣ
ጊዜ እጅግ ይሰብክ ጀመር፤ ዝናዉም ወጣና
ተገለጠ፤ በግልጥም ወደ ከተማ መግባት ተሳ
ነው፤ ነገር ግን በምድረ በዳ በውጭ ነበረ፤ ከየ
ስፍራዉም ሁሉ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

## ምዕራፍ ፪

### ሽባዉን ስለ ማዳኑ

(ማቴ. ፱፥፩-፰፤ ሉቃ. ፭፥፲፯-፳፮)

፩ዳግመኛም ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍር
ናሆም ከተማ ገባ፤ በቤትም እንዳለ ተሰማ።
፪በደጅ ያለው ቦታም እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ
ዎች ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፤ ወደ እርሱ
ለመጡትም ቃሉን ይነግራቸው ነበር። ፫አራት
ሰዎችም ሽባ የሆነ በሽተኛን በአልጋ ተሸክ
መው ወደ እርሱ አመጡለት። ፬ስለ ሕዝቡም
ብዛት ወደ እርሱ ማቅረብ ቢሳናቸው እርሱ ያለ
በትን የቤቱን ጣራ ነድለው ሽባዉን ከነአልጋው
አወረዱት። ፭ጌታችን ኢየሱስም እምነታቸውን
አይቶ ያን ሽባ፥ "ልጄ ሆይ ኀጢአትህ ተሰ
ረየልህ" አለው። ፮በዚያም ጻፎች ተቀምጠው
ነበሩ፤ በልባቸውም ዐሰቡ። ፯"ይህ ስለምን እን
ዲህ ያለ ስድብ ይናገራል? ከአንድ ከእግዚአብ
ሔር በቀር ኀጢአትን ማስተስረይ ማን ይች

፫ "እርሱም ከእነርሱ ጋር ነበር" የሚለው በግሪኩ የለም።
፩፥፳፪ ማቴ. ፯፥፳፰፥፳፱። ፩፥፴፱ ማቴ. ፬፥፳፫፤ ፱፥፴፭። ፩፥፵፬ ዘሌ. ፲፬፥ ፩-፴፪።

ላል?” አሉ። ፰ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ እን
ደሚያስቡ በመንፈሱ ዐውቆ እንዲህ አላቸው፥
“በልባችሁ እንዲህ ያለ ነገር ለምን ታስባላ
ችሁ? ፱ይህን ሽባ ኀጢአትህ ተሰረየልህ ከማ
ለትና፤ ወይም ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ
ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? ፲ነገር ግን
ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ሊያስተሰ
ርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥” ፲፩ዳግ
መኛ ሽባውን፥ “አንተን እልሃለሁ ተነሥ፥
አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ግባ” አለው።
፲፪ያንጊዜም ተነሥቶ አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ
ፊት ወጣ፤ ሁሉም አደነቁ፤ “እንዲህ ያለ ከቶ
አላየንም” እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑት።
፲፫ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ባሕር
ዳርቻ ዳግመኛ ሄደ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ
ሄዱና አስተማራቸው።

## ስለ ሌዊ

(ማቴ. ፱፥፱-፲፫፤ ሉቃ. ፭፥፳፯)

፲፬ከዚያም ሲያልፍ የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን
በቀረጥ መቀበያው ቦታ ተቀምጦ አገኘውና፥
“ተከተለኝ” አለው፤ ተነሥቶም ተከተለው።
፲፭ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ በሌዊ ቤት
በማዕድ ተቀመጠ፤ ብዙዎች ቀራጮችና ኀጢ
አተኞች ከጌታችን ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙ
ርቱ ጋር በማዕድ ተቀምጠው ነበር፤ የተከተ
ሉትም ብዙዎች ነበሩ። ፲፮ጻፎችና ፈሪሳውያ
ንም ከኀጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ሲበላና
ሲጠጣ አይተው፥ ደቀ መዛሙርቱን፥ “መምህ
ራችሁ ከኀጢአተኞችና ከቀራጮች ጋር ለምን
ይበላል? ይጠጣልም?” አሉአቸው። ፲፯ጌታችን
ኢየሱስም በሰማ ጊዜ እንዲህ አላቸው፥ “በሽ
ተኞች ባለ መድኀኒትን ይሹታል፤ ጤነኞች ግን
አይሹትም፤ ኀጥአንን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ
አልመጣሁምና።”

## ስለ ጾም የቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፱፥፲፬-፲፯፤ ሉቃ. ፭፥፴፫)

፲፰የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ከፈሪሳውያን
ወገን የሆኑትም ይጾሙ ነበር፤ ሄደውም፥ “የዮ
ሐንስ ደቀ መዛሙርትና የፈሪሳውያን ደቀ መዛ
ሙርት ይጾማሉ፤ የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን
ለምን አይጾሙም?” አሉት። ፲፱ጌታችን ኢየ
ሱስም እንዲህ አላቸው፥ “የሙሽራው ሚዜ
ዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ መጾም ይች
ላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ መጾም
አይችሉም። ፳ነገር ግን፥ ሙሽራውን ከእነርሱ
ለይተው የሚወስዱበት ቀን ይመጣል፤ ያን
ጊዜም ይጾማሉ። ፳፩በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ
እራፊ የሚጥፍ የለም፤ ቢጣፍ ግን አዲሱ መጣ
ፊያ አሮጌውን ይቀድደዋል፤ ቀዳዳውንም ያሰ
ፋዋል። ፳፪አዲስ የወይን ጠጅም በአሮጌ ረዋት
የሚጨምር የለም፤ አዲሱ የወይን ጠጅ አሮጌ
ውን ረዋት ይቀድደዋልና፤ ወይኑም ይፈስሳል፤
ረዋቱም ይቀደዳል፤ ነገር ግን፥ አዲሱን የወይን
ጠጅ በአዲስ ረዋት ያደርጉታል።”

## ስለ ሰንበት የቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፲፪፥፩-፰፤ ሉቃ. ፮፥፩-፭)

፳፫ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ በሰንበት
ቀን በእርሻ መካከል ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም
ከእርሱ ጋር በመንገድ ሲያልፉ እሸት ይቈ
ርጡ ጀመር። ፳፬ፈሪሳውያንም፥ “ደቀ መዛሙር
ትህ በሰንበት ሊደረግ የማይገባውን ለምን ያደር
ጋሉ?” አሉት። ፳፭ጌታችን ኢየሱስም፥ “ዳዊት
በተራበ ጊዜ፥ እርሱ አብረውት ከነበሩት ጋር
ያደረገውን አላነበባችሁምን? ፳፮አብያታር ሊቀ
ካህናት በነበረ ጊዜ ወደ ቤተ እግዚአብሔር
እንደ ገባና ለካህናት ብቻ እንጂ እርሱ ሊበላው
የማይገባውን የመሥዋዕቱን ኅብስት እንደ በላ፥
ከእርሱ ጋር ለነበሩትም እንደ ሰጣቸው አላነበባ
ችሁምን?” ፳፯ደግሞም እንዲህ አላቸው፥ “ሰን
በት ስለ ሰው ተፈጠረች እንጂ ሰው ስለ ሰን
በት አልተፈጠረም። ፳፰እንዲሁም የሰው ልጅ
ለሰንበት ጌታዋ ነው።”

## ምዕራፍ ፫

## እጁ ስለ ደረቀችው ሰው

(ማቴ. ፲፪፥፱-፲፬፤ ሉቃ. ፮፥፮-፲፩)

፩ዳግመኛም ወደ ምኵራብ ገባ፤ በዚያም
እጁ የሰለለች ሰው ነበር። ፪ሊከስሱትም በሰን
በት ይፈውሰው እንደ ሆነ ብለው ይጠባበቁት
ነበር። ፫ያን እጁ የሰለለችውን ሰውም “ተነ
ሣና በመካከል ቁም” አለው። ፬“በሰንበት መል
ካም ማድረግ ይገባልን? ወይስ ክፉ ማድረግ?
ነፍስ ማዳን? ወይስ መግደል?” አላቸው፤ እነ
ርሱ ግን ዝም አሉ። ፭ጌታችን ኢየሱስም ስለ
ልቡናቸው ድንዛዜ እያዘነ ተቈጥቶ ተመለከታ

፪፥፳፫ ዘዳ. ፳፫፥፳፭።　፪፥፳፭-፳፮ ፩ሳሙ. ፳፩፥፩-፮።　፪፥፳፮ ዘሌ. ፳፬፥፱።

ቸው፤ ያንም ሰው፥ “እጅህን ዘርጋ” አለው፤
እጁንም ዘረጋ፤ ዳነችም። ፮ያንጊዜም ፈሪሳው
ያን ወጥተው ሊገድሉት ከሄሮድስ ሰዎች ጋር
ተማከሩ።

## ስለ ሌሎች ተአምራት

፯ጌታችን ኢየሱስም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
ወደ ባሕር ሄደ፤ ከይሁዳ፥ ከገሊላም ብዙ
ሰዎች ተከተሉት። ፰እጅግ ብዙ ሰዎችም ያደ
ረገውን ሁሉ ሰምተው ከይሁዳ፥ ከኢየሩሳ
ሌም፥ ከኤዶምያስም፥ ከዮርዳኖስ ማዶ፥ ከጢ
ሮስና ከሲዶናም ወደ እርሱ መጡ። ፱ሰዎችም
እንዳይጋፉት፥ ታንኳን ያቆዩለት ዘንድ ደቀ
መዛሙርቱን አዘዛቸው። ፲ብዙ ሰዎችን አድ
ኗልና፥ ሥቃይ ያለባቸው ሁሉ እርሱን ለመዳ
ሰስ ይጋፉበት ነበር። ፲፩ርኩሳን መናፍስት የያ
ዟቸውም ባዩት ጊዜ፥ በፊቱ ወድቀው፥ “በእ
ውነት አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ” እያሉ
ጮኹ። ፲፪እንዳይገልጹትም እጅግ ገሠጻቸው።

## ሐዋርያትን ስለ መምረጡ

(ማቴ. ፲፥፩-፬፤ ሉቃ. ፮፥፲፪-፲፮)

፲፫ወደ ተራራም ወጣና የወደዳቸውን ጠራ፤
ወደ እርሱም መጡ። ፲፬ከእርሱም ጋር እንዲኖ
ሩና ለመስበክም ይልካቸው ዘንድ ዐሥራ ሁለ
ቱን መርጦ ሐዋርያት አላቸው። ፲፭አጋንንትን
እንዲያወጡ፥ ድውያንንም እንዲፈውሱ ሥል
ጣንን ሰጣቸው። ፲፮በየስማቸውም ጠራቸው፤
ስምዖንን “ጴጥሮስ” ብሎ ሰየመው። ፲፯የዘብ
ዴዎስ ልጅ ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንድም ዮሐ
ንስንም “ቦአኔርጌስ” ብሎ ሰየማቸው፤ “የነ
ጐድጓድ ልጆች” ማለት ነው። ፲፰እንድርያስ
ንና ፊልጶስን፥ በርተሎሜዎስንና ማቴዎስን፥
ቶማስንና የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብን፥ ታዴዎ
ስንና ቀነናዊውን ስምዖንንም፥ ፲፱አሳልፎ የሰ
ጠውን ያስቆሮቱን ይሁዳንም። ፳ወደ ቤትም
በገባ ጊዜ፥ እህል ይበላ ዘንድ እንኳ እስኪአ
ስቸግሩት ድረስ እንደ ገና ብዙ ሰዎች ተሰበ
ሰቡ። ፳፩ዘመዶቹም ሰምተው ልቡ ዘንጋ ብሎ
ታል ብለዋቸዋልና ሊይዙት መጡ። ፳፪ከኢ
የሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም፥ “ብዔል ዜቡል
ይዞታል፤ ደግሞም በአጋንንት አለቃ አጋን
ንትን ያወጣል” አሉ። ፳፫ጌታችን ኢየሱስም
ጠርቶ በምሳሌ እንዲህ አላቸው፥ “ሰይጣን
ሰይጣንን ሊያወጣ እንዴት ይችላል? ፳፬መንግ
ሥትም እርስ በርስዋ ከተለያየች ያች መንግ
ሥት አትጸናም። ፳፭ቤትም እርስ በርሱ ከተለ
ያየ ያ ቤት አይጸናም። ፳፮ሰይጣንም አንዱ በአ
ንዱ ላይ ቢነሣና እርስ በርሱ ቢለያይ መጨረሻ
ይሆናል እንጂ አይጸናም። ፳፯ኀይለኛውን አስቀ
ድሞ ካላሰረ ወደ ኀይለኛው ቤት መግባት፥ ገን
ዘቡንም መበርበር የሚችል የለም፤ ከዚያ በኋላ
ግን ቤቱን ይበረብራል።
፳፰“እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት፥ ስድ
ብም ሁሉ ለሰው ልጆች ይሰረይላቸዋል።
፳፱በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘ
ለዓለም ፍርድ ይፈረድበታል እንጂ አይሰረይለ
ትም።” ፴ርኩስ መንፈስ አለበት ብለዋልና።

## ፈቃዱን ስለሚያደርጉ

(ማቴ. ፲፪፥፵፮-፶፤ ሉቃ. ፰፥፲፱-፳፩)

፴፩እናቱና ወንድሞቹም መጥተው በውጭ
ቆመው ሊጠሩት ወደ እርሱ ላኩ። ፴፪ብዙዎ
ችም ሰዎች አብረውት ተቀምጠው ነበሩና፥
“እናትህና ወንድሞችህ እነሆ በውጭ ቆመ
ዋል፤ አንተንም ይፈልጉሃል” አሉት። ፴፫እር
ሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “እናቴ ማን
ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?” ፴፬በዙ
ሪያው ተቀምጠው ወደ ነበሩትም ተመል
ክቶ፥ “እነሆ፥ እናቴም ወንድሞቼም እነዚህ
ናቸው ፴፭የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ
ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜም፥ እኅቴም፥ እናቴም
ነውና።”

# ምዕራፍ ፬

## የዘሩ ምሳሌ

(ማቴ. ፲፫፥፩-፲፯፤ ሉቃ. ፰፥፬-፲)

፩ዳግመኛም በባሕር ዳር ያስተምር ጀመር፤
በባሕርም ወደ ታንኳ ገብቶ እስኪቀመጥ ድረስ
ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፤ ሰውም ሁሉ
በባሕሩ ዳር በምድር ላይ ነበር። ፪በምሳሌም
ብዙ አስተማራቸው፤ ሲያስተምራቸውም እን
ዲህ አላቸው፡- ፫“ስሙ፥ እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ
ወጣ። ፬ሲዘራም በመንገድ የወደቀ ዘር ነበረ፤
ወፎችም መጥተው በሉት። ፭አፈር በሌለበት
በጭንጫ ላይም የወደቀ ነበረ፤ መሬቱም ጥል
ቅነት አልነበረውምና ፈጥኖ በቀለ። ፮ፀሐይም
በወጣ ጊዜ ጠወለገ፤ ሥርም አልነበረውምና
ደረቀ። ፯በእሾህ መካከልም የወደቀ ዘር ነበረ፤

፫፥፱-፲ ማር ፬፥፩፤ ሉቃ. ፭፥፩-፫። ፫፥፳፪ ማቴ ፱፥፴፬፤ ፲፥፳፭። ፫፥፳፱ ሉቃ. ፲፪፥፲። ፬፥፩ ሉቃ. ፭፥፩-፫።

እሾሁም ወጣና አነቀው፤ ፍሬም አላፈራም።
፰በመልካም ምድር ላይም የወደቀ ዘር ነበረ፤
በቀለ፤ አደገም፤ ፍሬም ሰጠ፤ አንዱም ሠላሳ፥
ሌላውም ስድሳ፥ ሌላውም መቶ አፈራ። ፱የሚ
ሰማ ጆሮ ያለው ይስማ” አለ።

፲ብቻውንም በሆነ ጊዜ አብረውት የነበ
ሩት ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር
ምሳሌውን ጠየቁት። ፲፩እርሱም እንዲህ አላ
ቸው፥ “ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግ
ሥት ምስጢር ልታውቁ ተሰጥቶአችኋል፤
በውጭ ላሉት ግን፥ በምሳሌ ይሆንባቸዋል።
፲፪ማየትን አይተው እንዳያውቁ፥ መስማት
ንም ሰምተው እንዳያስተውሉ፥ እንዳይመ
ለሱ፥ ይቅርም እንዳልላቸው፥፩ ኀጢአታቸ
ውም እንዳይሰረይላቸው።” ፲፫እርሱም እን
ዲህ አላቸው፥ “ይህቺን ምሳሌ አታውቁ
ምን? እንግዲያ ምሳሌን ሁሉ እንዴት ታው
ቃላችሁ? ፲፬ዘሪው የእግዚአብሔርን ቃል የሚ
ዘራ ነው። ፲፭ቃል በተዘራበት መንገድ ያሉም
እነዚህ ናቸው፤ ቃሉን እንደ ሰሙ ያንጊዜ
ሰይጣን መጥቶ የተዘራውን ቃል ከልባቸው
ይወስዳል። ፲፮ዳግመኛም በጭንጫ ላይ የተ
ዘሩ፥ ቃሉን ሰምተው ፈጥነው በደስታ የሚ
ቀበሉት ናቸው። ፲፯ለጊዜው ነው እንጂ ሥር
የላቸውም፤ ስለዚህም ቃል መከራ ወይም
ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያውኑ ይክዳሉ። ፲፰በእ
ሾህም መካከል የተዘሩ ቃሉን የሚሰሙ እኒህ
ናቸው። ፲፱የዚህ ዓለም ዐሳብና የባለጠግነት
ማታለል፥ ሌላውም ምኞት ሁሉ ይገቡበ
ትና ቃሉን ያንቁታል፤ እርሱም አያፈራም።
፳በመልካም ምድር የተዘሩ ቃሉን ሰምተው
የሚቀበሉት ናቸው፤ አንዱ ሠላሳ፥ አንዱም
ስድሳ፥ አንዱም መቶ ቅንጣት የሚያፈሩ እነ
ዚህ ናቸው። ፳፩እንዲህም አላቸው፥ “መብ
ራትን አብርተው እንቅብ ሊደፉባት ወይም
ከአልጋ በታች ሊያኖሩአት የሚያመጡአት
አሉን? በመቅረዝዋ ላይ ሊያኖሩአት አይደ
ለምን? ፳፪የሚሸሸግ ስውር የለም፤ የማይገለ
ጥም የተሸፈነ የለም። ፳፫የሚሰማ ጆሮ ያለው
ይስማ።” ፳፬እንዲህም አላቸው፥ “የምትሰ
ሙትን አስተውሉ፤ በሰፈራችሁበት በዚያ
መስፈሪያ ይሰፍሩላችኋል፤ ይጨምሩላችኋ
ልም። ፳፭ላለው ይሰጡታል፤ ይጨምሩለታ
ልም፤ የሌለውን ግን፤ ያን ያለውን እንኳ
ይወስዱበታል።”

## ስለ ዘርና ስለ መከር ምሳሌ

፳፮እርሱም እንዲህ አላቸው፥ “የእግዚአብ
ሔር መንግሥት፪ መልካም ዘርን በምድሩ
ላይ እንደሚዘራ ሰው እንደዚሁ ናት። ፳፯እር
ሱም በሌሊት ይተኛል፤ በመዐልትም ይነ
ሣል፤ እርሱም ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል፤ ያድ
ጋልም፤ ፳፰ምድሪቱም ከእርስዋ ፍሬ ትሰጣ
ለች፤ መጀመሪያ ቡቃያን፥ ከዚህም በኋላ
ዛላን፥ ቀጥሎም በዛላው ላይ ፍጹም ሰብ
ልን ትሰጣለች። ፳፱ፍሬንም ፈጽሞ ባፈራ
ጊዜ ያንጊዜ መከር ደርሶአልና፤ ማጭድ
ይላካል።”

## ስለ ሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ

(ማቴ. ፲፫፥፴፩-፴፬፤ ሉቃ. ፲፫፥፲፰፡፲፱)

፴እንዲህም አለ፥ “የእግዚአብሔርን መን
ግሥት በምን እንመስላታለሁ? ምንስ ትመ
ስላለች? ፴፩እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናት፤
እርስዋም በምድር በተዘራች ጊዜ በምድር
ካሉ አዝርዕት ሁሉ ታንሳለች። ፴፪በተዘራችም
ጊዜ ትበቅላለች፤ ከአትክልትም ሁሉ ትበ
ልጣለች፤ የሰማይ ወፎችም በቅርንጫፎችዋ
በታች ሊጠለሉ እስከሚችሉ ድረስ ታላላቅ
ቅርንጫፎችን ታወጣለች።”
፴፫መስማትን በሚችሉበት መጠን እንዲህ
ባለ ብዙ ምሳሌ ቃሉን ነገራቸው። ፴፬ያለ
ምሳሌ ግን አልነገራቸውም። ለብቻቸውም
ሲሆኑ ለደቀ መዝሙርቱ ሁሉን ነገር ይተረ
ጒምላቸው ነበር። ፴፭ያንጊዜም ሲመሽ ደቀ
መዛሙርቱን፥ “ወደ ማዶ እንሻገር” አላ
ቸው። ፴፮ሕዝቡንም አሰናበተና በታንኳ ወሰ
ዱት፤ ከእነርሱም ጋር ሌሎች ታንኳዎች
ነበሩ። ፴፯ጽኑ ዐውሎ ነፋስም ተነሣ፤ ከሞገ
ዱም የተነሣ ውኃው ታንኳውን እስኪሞላው
ድረስ ማዕበሉ ወደ ታንኳው ይገባ ነበር።
፴፰እርሱ ግን በታንኳው በስተኋላ በኩል ተን
ተርሶ ተኝቶ ነበር፤ ቀስቅሰውም፥ “መምህር
ሆይ፥ ስንሞት አያሳዝንህምን?” አሉት።

---

፩ ግሪኩ “እንዳልፈውሳቸው” ይላል።

፪ ግሪኩ “መንግሥተ ሰማያት” ይላል።

፬፥፲፪ ኢሳ. ፮፥ ፱-፲። ፬፥፳፩ ማቴ. ፭፥፲፭፤ ሉቃ. ፲፩፥፴፫። ፬፥፳፪ ማቴ. ፲፥፳፮፤ ሉቃ. ፲፪፥፪።
፬፥፳፬ ማቴ ፯፥፪፤ ሉቃ. ፮፥፴፰። ፬፥፳፭ ማቴ. ፲፫፥፲፪፤ ፳፭፥፳፱፤ ሉቃ. ፲፱፥፳፮። ፬፥፳፱ ኢዩ. ፫፥፲፫።

### ባሕሩንና ነፋሳቱን ስለ መገሠጹ

(ማቴ. ፰፡፳፫-፳፯፤ ሉቃ. ፰፡፳፬-፳፭)

፴፱ተነሥቶም ነፋሱን ገሠጸው፤ ባሕርዋንም፥
"ዝም በዪ፥ ጸጥ በዪ" አላት፤ ነፋሱም ዝም
አለ፤ ፍጹም ጸጥታም ሆነ። ፵እንዲህም አላ
ቸው፥ "እናንተ ደካሞች፫ ምን ያስፈራችኋል?
እንዲህስ እምነት የላችሁም?" ፵፩ታላቅ ፍርሀት
ንም ፈሩ፤ እርስ በርሳቸውም፥ "እንግዲህ ባሕ
ርም፥ ነፋስም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው?"
ተባባሉ።

## ምዕራፍ ፭

### ሌጌዎን ያደረበትን በሽተኛ እንደ ፈወሰው

(ማቴ. ፰፡፳፰-፴፬፤ ሉቃ. ፰፡፳፮)

፩ወደ ባሕር ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን አገር
ደረሱ፤ ፪ከታንኳውም በወረደ ጊዜ ርኩስ መን
ፈስ ያደረበት ሰው ከመቃብር ወጥቶ ተገናኘው።
፫እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፤ ማንም በእግር
ብረት እንኳ ቢሆን ያሥረው ዘንድ አይችልም
ነበር። ፬ዘወትር በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታ
ሰር ነበርና፥ ነገር ግን እግር ብረቱን ይሰብርና
ሰንሰለቱን ይቀጠቅጥ ነበር፤ ሊያሸንፈውም የሚ
ችል አልነበረም። ፭ዘወትርም በመቃብርና በተ
ራራ፥ በመዐልትና በሌሊት ይጮህ ነበር፤ ሰውነ
ቱንም በባልጩት ይቈርጥ ነበር። ፮ጌታችን ኢየ
ሱስንም ከሩቅ ባየው ጊዜ ሮጦ ሰገደለት። ፯በታ
ላቅ ድምፅም እየጮኸ፥ "የልዑል እግዚአብሔር
ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?
እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር አምልሃለሁ"
አለው። ፰ያን ርኩስ መንፈስ ከእርሱ ውጣ
ብሎት ነበርና። ፱ጌታችን ኢየሱስም፥ "ስምህ
ማነው?" ብሎ ጠየቀው፤ እርሱም፥ "ስሜ ሌጌ
ዎን ነው፤ እኛ ብዙዎች ነንና" አለው። ፲ከሀ
ገርም አስወጥቶ እንዳይሰድደው አብዝቶ ማለ
ደው። ፲፩ከዚያም በተራራው አጠገብ ብዙ የዕ
ሪያ መንጋ ተሰማርቶ ነበር። ፲፪እነዚያ አጋንን
ትም፥ "እናድርባቸው ዘንድ ወደ ዕሪያዎች ስደ
ደን" ብለው በብዙ ማለዱት። ፲፫ጌታችን ኢየሱ
ስም ፈቀደላቸው፤ እነዚያ ርኩሳን መናፍስትም
ወጥተው ወደ ዕሪያዎች ገቡ፤ መንጋዎቹም በር
ግገው ወደ ባሕሩ ተወረወሩ፤ እነርሱም ሁለት
ሺህ ያህል ነበሩ፤ በባሕሩ ውስጥም ሰጠሙ።
፲፬እረኞችም ሸሽተው በከተሞችና በመ
ንደሮች ተናገሩ፤ እነርሱም የሆነውን ሊያዩ
መጡ። ፲፭ወደ ጌታችን ኢየሱስም መጡ፤ ጋኔን
የያዘውን፥ ሌጌዎንም የነበረበትን ሰው ልቡ
ተመልሶለት፥ ልብሱንም ለብሶ ተቀምጦ አዩ
ትና ፈሩ። ፲፮ያዩ ሰዎችም ጋኔን ለያዘው ሰው
የሆነውንና በዕሪያዎቹም የተደረገውን ነገሩአ
ቸው። ፲፯ከሀገራቸውም ይወጣ ዘንድ ይማል
ዱት ጀመሩ። ፲፰ወደ ታንኳው በወጣ ጊዜም
ያ ጋኔን የወጣለት ሰው ከእርሱ ጋር ይኖር
ዘንድ ማለደው። ፲፱ጌታችን ኢየሱስም ከለከ
ለው፤ "ወደ ቤትህ ወደ ወገኖችህ ሂድ፤ እግ
ዚአብሔር ያደረገልህንም ታላቅ ነገር ሁሉ፥
ይቅር እንዳለህም ተናገር" አለው። ፳ሄዶም
ጌታችን ኢየሱስ ያደረገለትን ሁሉ በዐሥሩ ከተ
ሞች ይሰብክ ጀመር፤ ሁሉም አደነቁ። ፳፩ዳግ
መኛም፥ ጌታችን ኢየሱስ በታንኳው ወደ ማዶ
ተሻገረ፤ ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፤
በባሕር ዳርም ነበረ።

### ስለ ምኵራብ ሹም

(ማቴ. ፱፡፲፰-፳፮፤ ሉቃ. ፰፡፵-፶፮)

፳፪እነሆ፥ ስሙ ኢያኢሮስ የተባለ የምኵራብ
ሹም የነበረ አንድ ሰው ወደ እርሱ መጣና
አገኘው፤ ከእግሩ በታችም ወድቆ ሰገደለት።
፳፫"ልጄ ልትሞት ደርሳለች፤ ነገር ግን ና እጅ
ህን ጫንባት፤ ትድናለችም" እያለ አብዝቶ
ማለደው። ፳፬ጌታችን ኢየሱስም ከእርሱ ጋር
ሄደ፤ ብዙ ሰዎችም ተከተሉት፤ ይጋፉትም
ነበር።

### ደም ይፈስሳት ስለነበረችው ሴት

፳፭ከዐሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም ይፈ
ስሳት የነበረች ሴት ነበረች። ፳፮ከብዙዎች ባለ
መድኀኒቶችም እጅግ ደከመች፤ ገንዘብዋንም
ሁሉ ሰጥታ ጨረሰች፤ ነገር ግን እጅግ ባሰባት
እንጂ ምንም የጠቀማት የለም። ፳፯የጌታችን
ኢየሱስን ነገር በሰማች ጊዜ መጣችና በሰው
መኃል ገብታ በስተኋላው የልብሱን ጫፍ ዳሰ
ሰች። ፳፰የልብሱን ጫፍ የዳሰስሁ እንደ ሆነ
እድናለሁ ብላለችና። ፳፱ወዲያውም የደምዋ
ምንጭ ደረቀ፤ ከደዌዋም እንደ ዳነች ራስዋ
ዐወቀች። ፴ጌታችን ኢየሱስም ኀይል ከእርሱ
እንደ ወጣ ዐውቆ፥ ወደ ሰዎች መለስ ብሎ፥

---

፫ "እናንተ ደካሞች" የሚለው በግሪኩ የለም።

፭፡፩-፳ ማቴ. ፰፡፳፰-፴፬፤ ሉቃ. ፰፡፳፮-፴፱። ፭፡፳፩-፵፫ ማቴ. ፱፡፲፰-፳፮፤ ሉቃ. ፰፡፵-፶፮።

"ልብሴን ማን ዳሰሰ?" አላቸው። ፴፩ደቀ መዛ
ሙርቱም፥ "ሕዝቡ ሲጋፋህ ታያለህ፤ አንተ
ግን ማን ዳሰሰኝ? ትላለህ" አሉት። ፴፪ይህንም
ያደረገውን ያይ ዘንድ ዘወር አለ። ፴፫ሴቲቱም
የተደረገላትን ስላወቀች ፈራች፤ እጅግም ተን
ቀጠቀጠች፤ ወደ ጌታችን ኢየሱስም መጥታ
ሰገደችለት፤ እውነቱንም ሁሉ ነገረችው ፴፬እር
ሱም፥ "ልጄ ሆይ፥ ሃይማኖትሽ አዳነችሽ፥ በሰ
ላም ሂጂ፤ ከደዌሽም ተፈወሺ" አላት።

### ስለ ምኩራቡ ሹም ልጅ

፴፭ከእርስዋ ጋር ሲነጋገርም ሰዎች ከምኩ
ራቡ ሹም ቤት መጥተው፥ "ልጅህ ሞታለች፤
እንግዲህ መምህርን አታድክመው" አሉት።
፴፮ጌታችን ኢየሱስም ሲያነጋግሩት በሰማ ጊዜ፥
የምኩራቡን ሹም፥ "እመን እንጂ አትፍራ"
አለው። ፴፯ከጴጥሮስና ከያዕቆብ፥ ከያዕቆብ ወን
ድም ከዮሐንስም በቀር የሚከተለው ማንም እን
ዳይኖር ከለከለ። ፴፰ወደ ምኩራቡ ሹም ቤት
በገባ ጊዜም ሲታወኩና፥ ሲያለቅሱ፥ እጅግም
ሲጮኹ አገኛቸው። ፴፱ገብቶም፥ "ለምን ትጮ
ኻላችሁ? ለምንስ ታለቅሳላችሁ? ልጅቱስ ተኝ
ታለች እንጂ አልሞተችም" አላቸው። ፵በጣ
ምም ሳቁበት፤ እርሱ ግን ሁሉን አስወጥቶ የብ
ላቴናይቱን አባትና እናት፥ ከእርሱ ጋር የነበ
ሩትንም ይዞአቸው ብላቴናይቱ ወደ አለችበት
ገባ። ፵፩የብላቴናይቱንም እጅ ይዞ፥ "ጣሊታ፡፩
ቁሚ" አላት፤ ትርጓሜውም "አንቺ ብላቴና
ተነሺ" ማለት ነው። ፵፪ያንጊዜም ያቺ ብላ
ቴና ተነሥታ ወዲያና ወዲህ አለች፤ ዕድሜ
ዋም ዐሥራ ሁለት ዓመት ነበር፤ ያንጊዜም
ታላቅ መደነቅን ተደነቁ። ፵፫ይህንም የሚያውቅ
ማንም እንዳይኖር በብዙ መከራቸው፤ የምትበ
ላውንም እንዲሰጡአት አዘዘ።

## ምዕራፍ ፮

### በናዝሬት ስለ ማስተማሩ

(ማቴ. ፲፫፥፶፫-፶፰፤ ሉቃ. ፬፥፲፮)

፩ከዚያም ወጥቶ ወደ ሀገሩ ገባ፤ ደቀ መዛሙ
ርቱም ተከተሉት። ፪በሰንበትም በምኩራብ ያስ
ተምር ጀመረ፤ ብዙዎችም ያዳምጡት ነበር፤
"ይህ ሁሉ ነገር ለእርሱ ከየት ተሰጠው? የተ
ሰጠችው ይህች ጥበብስ ምንድን ናት? በእ
ጁም የሚደረገው ይህ ኀይል ምንድን ነው?"
እያሉ ያደንቁ ነበር። ፫"ይህ ጸራቢው የማርያም
ልጅ አይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ፥
ይሁዳና ስምዖንስ አይደሉምን? እኅቶቹስ ሁሉ
በእኛ ዘንድ ያሉ አይደለምን?" እያሉ ይሰናከ
ሉበት ነበር። ፬ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላ
ቸው፥ "በሀገሩ፥ በወገኑና በዘመዶቹ ካልሆነ
በቀር ነቢይ አይናቅም።" ፭እጁን ጭኖ ካዳ
ናቸው ከጥቂት ድውያንም በቀር በዚያ ተአ
ምራትን አላደረገም። ፮ስለ አለማመናቸውም
ተደነቀ፤ በመንደሮችም እያስተማረ ይመላለስ
ነበር።

### ያስተምሩ ዘንድ ሐዋርያትን ስለ መላኩ

(ማቴ. ፲፥፭-፲፭፤ ሉቃ. ፱፥፩-፮)

፯ዐሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠርቶ ሁለት
ሁለት አድርጎ ላካቸው፤ በርኩሳን መናፍስት
ላይም ሥልጣን ሰጣቸው። ፰ለመንገድም ከበ
ትር ብቻ በቀር እንጀራም ቢሆን፥ከረጢትም
ቢሆን፥ መሐለቅም በመታጠቂያቸው እንዳይዙ
አዘዛቸው። ፱በእግራቸው ካለው ጫማ በቀርም
ሁለት ልብስ እንዳይለብሱ አዘዛቸው። ፲እንዲ
ህም አላቸው፥ "ከዚያ እስክትወጡ ድረስ በገ
ባችሁበት ቤት በዚያው ተቀመጡ። ፲፩ከማይ
ቀበሉአችሁና ከማይሰሙአችሁ ሀገርም ከዚያ
ወጥታችሁ ምስክር ሊሆንባቸው የእግራች
ሁን ትቢያ አራግፉ፤ እውነት እላችኋለሁ፥
ከዚያች ከተማ ይልቅ በፍርድ ቀን ሰዶምና
ገሞራ ዕረፍትን ያገኛሉ።" ፲፪ወጥተውም ሁሉ
ንስሓ ይገቡ ዘንድ ሰበኩ። ፲፫ብዙ አጋንንት
ንም አወጡ፤ ብዙ ድውያንንም ዘይት እየቀቡ
ፈወሱአቸው።

### ስለ ሄሮድስና ስለ መጥምቁ ዮሐንስ

(ማቴ. ፲፬፥፩-፲፪፤ ሉቃ. ፱፥፯-፱)

፲፬ንጉሥ ሄሮድስም ሰማ፤"ስሙ ግልጥ ሆኖአ
ልና፥ መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ተለይቶ ተነ
ሥቶአል፤ ስለዚህም ኀይል ይረዳዋል"፩ አለ።
፲፭"ኤልያስ ነው ያሉም ነበሩ፥ ከነቢያት እንደ
አንዱ ነቢይ ነው" ያሉም ነበሩ፤ ፲፮ሄሮድስ

---

፩ ግእዙ "ጣቢታ" ይላል።

፩ ግሪኩ "በእርሱ ኀይል ይደረጋል" ይላል።

፮፥፬ ዮሐ. ፬፥፵፬። ፮፥፯-፲፩ ሉቃ. ፲፥ ፬-፲፩። ፮፥፲፩ ሐ.ሥ. ፲፫፥፶፩። ፮፥፲፫ ያዕ. ፭፥፲፬።
፮፥፲፬-፲፭ ማቴ. ፲፮፥፲፬፤ ማር. ፰፥፳፰፤ ሉቃ. ፱፥፲፱።

ግን ሰምቶ፥ "ይህ እኔ ራሱን ያስቈረጥሁት
ዮሐንስ ነው፤ እርሱ ከሙታን ተለይቶ ተነሥ
ቶአል" አለ። ፲፯ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶ
ስን ሚስት ሄሮድያዳን አግብቶ ነበርና በእር
ስዋ ምክንያት ጭፍሮቹን ልኮ ዮሐንስን ይዞ
አስሮት ነበር፤ ፲፰ዮሐንስ ሄሮድስን፥ "የወን
ድምህን ሚስት ልታገባ አይገባህም" ይለው
ነበርና። ፲፱ሄሮድያዳም ጠልታው ነበርና ልታ
ስገድለው ትሻ ነበር፤ ነገር ግን አልተቻላ
ትም። ፳ሄሮድስም ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ
ሆነ ያውቅ ነበርና ዮሐንስን ይፈራውና ይጠ
ባበቀው ነበር፤ በእርሱም ዘንድ ብዙ ይሰማ
ነበር፤ ደስ እያለውም ይሰማው ነበር። ፳፩ሄሮ
ድስም የተወለደባትን ቀን በዓል በአደረገ ጊዜ
መኳንንቱንና የሻለቆቹን፤ የገሊላንም ታላላቅ
ሰዎች ግብር አገባ። ፳፪የሄሮድያዳ ልጅም ምቹ
ጊዜ ሆነላትና ገብታ ዘፈነች፤ ሄሮድስንና ከእ
ርሱ ጋር በማዕድ የተቀመጡትንም ደስ አሰኘ
ቻቸው፤ ንጉሡም ብላቴናይቱን፥ "የምትሺ
ውን ለምኝኝ፥ እሰጥሻለሁ" አላት። ፳፫እስከ
መንግሥቱ እኩሌታ ድረስ ቢሆንም እንኳ የለ
መነችውን ሁሉ ሊሰጣት ማለላት። ፳፬ወጥታም
እናቷን፥ "ምን ልለምነው?" አለቻት፤ እር
ስዋም፥ "የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ" አለ
ቻት። ፳፭ያንጊዜም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ፥
"የመጥምቁ ዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን እን
ድትሰጠኝ እሻለሁ" ብላ ለመነችው። ፳፮ንጉ
ሡም እጅግ አዘነ፤ ስለ መሐላው፥ ከእርሱም
ጋር በማዕድ ስለ ተቀመጡት ሰዎች እንቢ
ሊላት አልወደደም። ፳፯ያንጊዜም ንጉሡ ከጭ
ፍሮቹ ባለ ወግ ልኮ ራሱን እንዲያመጣ አዘዘ።
ሄዶም የዮሐንስን ራስ በግዞት ቤት ቈረጠ፤
፳፰ራሱንም በወጭት አምጥቶ ለዚያች ብላቴና
ሰጣት፤ ብላቴናይቱም ለእናቷ ሰጠች። ፳፱ደቀ
መዛሙርቱም በሰሙ ጊዜ፤ ሄዱና የዮሐንስን
በድን ወስደው ቀበሩት።

### ሐዋርያት ወደ ጌታ ስለ መመለሳቸው

(ማቴ. ፲፬፥፲፫-፳፩፤ ዮሐ. ፮፥፩-፲፬)

፴ሐዋርያትም ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ
ተሰብስበው የሠሩትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገ
ሩት። ፴፩"ኑ ለብቻችን ወደ ምድረ በዳ እንው
ጣና ጥቂት ዕረፉ"፬ አላቸው፤ የሚመጡና የሚ
ሄዱ ብዙዎች ነበሩና፤ እህልም ይበሉ ዘንድ
እንኳ ጊዜ አላገኙም። ፴፪ብቻቸውንም በታንኳ
ወደ ምድረ በዳ ሄዱ። ፴፫ብዙዎቹም ሲሄዱ
አይተው ዐወቁአቸው፤ ከከተሞችም ሁሉ በእ
ግር እየሮጡ ቀደሙአቸው፤ ወደ እርሱም
መጡ።

### ሁለቱን ዓሣዎችና አምስቱን እንጀራ ስለ መባረኩ

፴፬ጌታችን ኢየሱስም በወጣ ጊዜ፥ ብዙ ሰዎ
ችን አየና እረኛ እንደሌላቸው በጎች ስለ ነበሩ
አዘነላቸው፤ ብዙም ያስተምራቸው ጀመረ።
፴፭ከብዙ ሰዓት በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ወደ
እርሱ ቀርበው እንዲህ አሉት፥ "ይህ ስፍራ
ምድረ በዳ ነው፤ ጊዜውም ፈጽሞ መሽቶአል።
፴፮የሚበሉትም የላቸውምና በዙሪያ ወዳሉ ገጠ
ሮችና መንደሮች ሄደው እንጀራ ለራሳቸው
ይገዙ ዘንድ ሕዝቡን አሰናብት።" ፴፯እርሱም
መልሶ፥ "እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው"
አላቸው፤ ደቀ መዛሙርቱም፥ "ይበሉ ዘንድ
እንድንሰጣቸው በሁለት መቶ ዲናር እንጀራ
ለመግዛት እንሂድን?" አሉት። ፴፰"ሂዱና
ስንት እንጀራ እንዳላችሁ እዩ" አላቸው፤
አይተውም፥ "አምስት እንጀራ ሁለትም ዓሣ
አለን" አሉት። ፴፱ሁሉንም በለመለመ መስክ
ላይ በየክፍሉ እንዲያስቀምጧቸው አዘዛቸው።
፵መቶ መቶውና አምሳ አምሳው ሆነው በተራ
ተቀመጡ። ፵፩አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ
ይዞ ወደ ሰማይ አየ፤ እንጀራውንም ባረከ፤
ቈርሶም እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ
ሰጣቸው፤ ሁለቱንም ዓሣዎች ለሁሉ ከፈለ።
፵፪ሁሉም በልተው ጠገቡ። ፵፫ከቍርስራሹም፥
ከዓሣውም ደግሞ ዐሥራ ሁለት መሶብ የሞላ
አነሡ። ፵፬እንጀራውንም የበሉት ወንዶች አም
ስት ሺህ ነበሩ።

### በባሕር ላይ ስለ መሄዱ

(ማቴ. ፲፬፥፳፪-፴፫፤ ዮሐ. ፮፥፲፮-፳፩)

፵፭ያንጊዜም እርሱ ሕዝቡን እስኪያሰናብት
ድረስ ወደ ታንኳው ገብተው ወደ ማዶ ወደ
ቤተ ሳይዳ ይቀድሙት ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን
ግድ አላቸው። ፵፮እነርሱንም አሰናብቶ ከዚያ
ሄደ፤፭ ሊጸልይም ወደ ተራራ ወጣ። ፵፯በመ

---

፬ ግሪኩ "ለብቻችሁ ወደ ምድረ በዳ ውጡ" ይላል።

፭ "ከዚያ ሄደ" የሚለው በግሪኩ የለም።

፮፥፲፯-፲፰ ሉቃ. ፫፥፲፱-፳። ፮፥፴፬ ዘኍ. ፳፯፥፲፯፤ ፩ነገ. ፳፪፥፲፯፤ ፪ዜ.መ. ፲፰፥፲፮፤ ሕዝ. ፴፬፥፭፤ ማቴ. ፱፥፴፮።

ሽም ጊዜ ታንኳይቱ በባሕር መካከል ነበረች፤
እርሱ ግን ብቻውን በየብስ ላይ ነበረ። ፵፰ ነፋስ
ከፊታቸው ነበርና እየቀዘፉ ሲጨነቁ አያቸው፤
በአራተኛው ክፍለ ሌሊትም ጌታችን ኢየሱስ
ባሕሩን እየረገጠ ወደ እነርሱ መጣ፤ ሊያልፉ
ቸውም ይወድድ ነበር። ፵፱ በባሕር ላይ ሲሄ
ድም ባዩት ጊዜ ምትሀት መስሏቸው ጮኹ።
፶ ሁሉም አዩትና ደነገጡ፤ ያንጊዜም ተናገራ
ቸውና “አይዞአችሁ እኔ ነኝ አትፍሩ” አላ
ቸው። ፶፩ ወደ እነርሱም ወደ ታንኳው ውስጥ
ገባ፤ ነፋሱም ፀጥ አለ፤ እጅግም ተገረሙ።
፶፪ ልባቸውም ደንዝዞ ነበርና ስለ እንጀራው አላ
ስተዋሉም ነበር።

### ጌታችን በጌንሴሬጥ ተአምራትን ስለ ማድረጉ
(ማቴ. ፲፬፥፴፬-፴፮)

፶፫ ተሻግረውም ወደ ጌንሴሬጥ ምድር ደረሱ፤
ታንኳቸውንም በዚያ አስጠጉ። ፶፬ ከታንኳው
ሲወጡም ወዲያውኑ የዚያች ሀገር ሰዎች ዐወ
ቁት። ፶፭ በየመንደሩም ሁሉ ሮጡ፤ በሽተኞች
ንም በአልጋ አመጡ፤ እርሱም በዚያ እንዳለ
ወደ ሰሙበት ቦታ ወሰዱ። ፶፮ በገባበትም ቦታ
ሁሉ በየከተማው፥ በየመንደሩና በየገጠሩ በሽ
ተኞችን በገበያዎች ያስቀምጡ ነበር፤ የልብሱ
ንም ጫፍ እንዲዳስሱ ይለምኑት ነበር፤ የዳሰ
ሱትም ሁሉ ይድኑ ነበር።

## ምዕራፍ ፯

### ጌታችን ፈሪሳውያንን ስለ መገሥጹ
(ማቴ. ፲፭፥፩-፳)

፩ ፈሪሳውያንና ከጻፎች ወገን ከኢየሩሳሌም
የመጡ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ፪ ከደቀ መዛሙ
ርቱም አንዳንዶችን እጃቸውን ሳይታጠቡ እን
ጀራ ሲበሉ አዩአቸው። ፫ ፈሪሳውያንና አይ
ሁድም ሁሉ የሽማግሎችን ወግ ስለሚጠ
ብቁ እጃቸውን ደኅና አድርገው ካልታጠቡ
እህል አይበሉም ነበር። ፬ ከገበያ የገዙትንም
በውኃ ካላጠቡ አይበሉም ነበር፤ [፩] ሌላም
የሚጠብቁት ብዙ ሥርዐት ነበር፤ ጽዋውንና
ማድጋውን፥ የናስ ዕቃውንና አልጋውንም
ያጥቡ ነበር። ፭ ጻፎችና ፈሪሳውያንም፥ “ደቀ
መዛሙርትህ ለምን እንደ ሽማግሎች ወግ
አይሄዱም? እጃቸውንስ ሳይታጠቡ ለምን
እህል ይበላሉ?” ብለው ጠየቁት። ፮ ጌታችን
ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “እና
ንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ በእናንተ ላይ መል
ካም ተናግሮአል፤ እንደ ተጻፈ ‘እነዚህ ሕዝ
ቦች በከንፈራቸው ያከብሩኛል፤ በልባቸው
ግን ከእኔ በጣም ይርቃሉ። ፯ የሰው ሥርዐት
የሆነ ትምህርትን እያስተማሩ በከንቱ ያመል
ኩኛል።’ ፰ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ
የሰውን ወግ ታጠብቃላችሁ፥ ጽዋን ማድጋ
ንም ማጠብን፥ ሌላውንም ይህን የመሰለውን
ሁሉ ታደርጋላችሁ።” ፱ ደግሞ እንዲህ አላ
ቸው፥ “የራሳችሁን ወግ ትጠብቁ ዘንድ የእ
ግዚአብሔርን ትእዛዝ ልታፈርሱ ይገባልን?
፲ ሙሴም አባትህንና እናትህን አክብር፤ በአባ
ቱና በእናቱ ላይ ክፉ ቃልን የተናገረ ሞትን
ይሙት ብሎአችሁ ነበር። ፲፩ እናንተ ግን ትላ
ላችሁ፡- ሰው አባቱን ወይም እናቱን ከእኔ
የተጠቀምህበት ቊርባን ማለት መባ ነው
ቢል፥ ፲፪ ለአባቱ ወይም ለእናቱ ምንም እን
ዲያደርግ አትፈቅዱለትም። ፲፫ ስለ ሥራችሁ
ትም ወጋችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራ
ላችሁ፤ ዳግመኛም ይህን የመሰለው የምት
ሠሩት ብዙ ነው።”

፲፬ ዳግመኛም ሕዝቡን ጠርቶ እንዲህ አላ
ቸው፥ “ሁላችሁም ስሙ፤ አስተውሉም።
፲፭ ከሰው ልብ የሚወጣው እርሱ ሰውን ያረ
ክሰዋል እንጂ ከውጭ ወደ ሰው አፍ የሚገ
ባው ሊያረክሰው የሚችል አይደለም። ፲፮ የሚ
ሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።” ፲፯ ከሕዝቡም ተለ
ይቶ ወደ ቤት በገባ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ
ምሳሌውን ጠየቁት። ፲፰ እርሱም እንዲህ አላ
ቸው፥ “እናንተ ደግሞ እንዲህ አታስተውሉ
ምን? ከውጭ ወደ ሰው አፍ የሚገባው ሁሉ
ሰውን ሊያረክሰው እንደማይችል አታውቁ
ምን? ፲፱ ወደ ሆዱ ብቻ እንጂ ወደ ልቡ አይገ
ባምና፤ ምግቡንም ሁሉ እያጣራ ወደ ውጭ
ያፈስሳል።” ፳ እንዲህም አላቸው፥ “ከሰው
የሚወጣው ሰውን የሚያረክሰው እርሱ ነው።
፳፩ ከሰው ልብ ውስጥ ክፉ ዐሳብ ሁሉ ይወጣ
ልና፤ ይኸውም ዝሙት፥ ስርቆት፥ መግደል፥
፳፪ ማመንዘር፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥
መዳራት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ምቀኝነት፥ ስን
ፍና ነው። ፳፫ ከውስጥ የሚወጣው ይህ ሁሉ
ክፉ ነገር ሰውን ያረክሰዋል።”

---

፩ ግሪኩ “ከገበያ ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም ...” ይላል።

፯፥፮-፯ ኢሳ. ፳፱፥፲፫። ፯፥፲ ዘፀ. ፳፥፲፪፤ ፳፩፥፲፯፤ ዘሌ. ፳፥፱፤ ዘዳ. ፭፥፲፮።

## ስለ ሲሮፊኒቃዊት ሴት
(ማቴ. ፲፭፥፳፩-፳፰)

፳፬ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ ተነሥቶ ወደ
ጢሮስና ወደ ሲዶና ሀገር ሄደ፤ ወደ ቤትም
ገባ፤ ማንም ሊያውቀው አልወደደም ነበር፤
ነገር ግን ሊሰወር አልቻለም። ፳፭ያንጊዜም
ልጅዋን ርኩስ መንፈስ የያዘባት አንዲት ሴት
የእርሱን ነገር ሰምታ መጣች፤ ገብታም ከእ
ግሩ በታች ወድቃ ሰገደችለት። ፳፮ሴቲቱም
አረማዊት ነበረች፤ በትውልዷም ከሶርያና ከፊ
ንቄ ወገን ነበረች፤ ከልጅዋም ጋኔኑን ያወ
ጣላት ዘንድ ለመነችው። ፳፯ጌታችን ኢየ
ሱስ ግን፥ “ተዪ፤ በመጀመሪያ ልጆች ይጥ
ገቡ፤ የልጆችን እንጀራ ነጥቆ ለውሾች መስ
ጠት መልካም አይደለምና” አላት። ፳፰እር
ስዋም መልሳ፥ “አዎን፥ ጌታ ሆይ፥ ውሾ
ችም እኮ ከልጆች የወደቀውን ፍርፋሪ ከገ
በታ በታች ሆነው ይበላሉ” አለችው። ፳፱እር
ሱም፥ “ሂጂ፤ ስለዚህ አነጋገርሽም ጋኔኑ ከል
ጅሽ ወጥቶአል” አላት። ፴ወደ ቤቷም ተመ
ለሰች፤ ልጅዋንም ጋኔኑ ለቆአት፥ ልብስዋ
ንም ለብሳ፥፩ በአልጋዋም ላይ ተቀምጣ አገ
ኘቻት።

### ጌታ ዲዳውንና ደንቆሮውን ስለ መፈወሱ

፴፩ዳግመኛም ከጢሮስ አልፎ በሲዶና
በኩል ዐሥር ከተማ በሚባል ሀገር መካ
ከል ወደ ገሊላ ባሕር ሄደ። ፴፪ዲዳና ደን
ቆሮ የሆነ ሰውም አምጥተው እጁን እንዲ
ጭንበት ማለዱት። ፴፫ብቻውንም ከሰዎች
ፈቀቅ አደረገው፤ ጣቶቹንም ወደ ጆሮዎቹ
አገባ፤ ምራቁንም እንትፍ ብሎ ምላሱን ዳሰ
ሰው። ፴፬ወደ ሰማይም ተመልክቶ አዘነና፤
“ኤፍታህ” አለ፤ ይህም “ ተከፈት” ማለት
ነው። ፴፭ወዲያውኑም ጆሮዎቹ ተከፈቱ፤ የም
ላሱም እስራት ተፈታና አስተካክሎ ተናገረ።
፴፮ለማንም እንዳይነግሩ ከለከላቸው፤ ነገር
ግን እርሱ የሚከለክላቸውን ያህል እነርሱ
ደግሞ ይናገሩለት ነበር። ፴፯እጅግም ተደነ
ቁና፥ “ሁሉን ደኅና አድርጎአል፤ ደንቆሮ
ችም እንዲሰሙ፥ ዲዳዎችም እንዲናገሩ ያደ
ርጋል” አሉ።

## ምዕራፍ ፰

### ጌታችን ሁለቱን ዓሣዎችና ሰባቱን እንጀራ ስለ ማበርከቱ
(ማቴ. ፲፭፥፴፪-፴፱)

፩በዚያም ወራት ደግሞ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤
የሚበሉትም አልነበራቸውም፤ ደቀ መዛሙርቱ
ንም ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ ፪“እነዚህ ሰዎች
ያሳዝኑኛል፤ እነሆ፥ በእኔ ዘንድ ሦስት ቀን
ቈይተዋልና፤ የሚበሉትም የላቸውምና። ፫እን
ደራባቸው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ባሰናብ
ታቸውም በመንገድ ይደክማሉ፤ ከእነርሱም
መካከል ከሩቅ የመጡ አሉ።” ፬ደቀ መዛሙ
ርቱም፥ “ይህን ሁሉ ሕዝብ በዚህ በምድረ
በዳ እንጀራ ማጥገብ ማን ይችላል?” አሉት።
፭እርሱም “ስንት እንጀራ አላችሁ?” ብሎ ጠየ
ቃቸው፤ እነርሱም “ሰባት” አሉት። ፮ሕዝ
ቡንም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዛቸው፤
ሰባቱንም እንጀራ ይዞ አመሰገነ፤ ቈርሶም እን
ዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፤
እነርሱም ለሰዎች አቀረቡ። ፯ጥቂት ዓሣም ነበ
ራቸውና እርሱንም ባርኮ፥ እንዲያቀርቡላቸው
አዘዘ። ፰በልተውም ጠገቡ፤ ያነሡትም የተረ
ፈው ቍርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሞላ። ፱የበሉ
ትም አራት ሺህ ያህል ነበሩ፤ ከዚህም በኋላ
አሰናበታቸው። ፲ወዲያውም ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር በታንኳው ገብቶ ወደ ድልማኑታ አው
ራጃ ሄደ።

### ከሰማይ ምልክትን ስለሚሹ ሰዎች
(ማቴ. ፲፮፥፩-፬)

፲፩ፈሪሳውያንም ወጥተው ይከራከሩት
ጀመር፤ ሊፈታተኑትም ከሰማይ ምልክትን
ጠየቁት። ፲፪በልቡም አዝኖ፥ “ይህች ትው
ልድ ምልክትን ለምን ትሻለች? እውነት እላ
ችኋለሁ፥ ለዚች ትውልድ ምልክት አይሰጣ
ትም” አለ።

### ስለ ፈሪሳውያን እርሾ
(ማቴ. ፲፮፥፭-፲፪)

፲፫ትቶአቸውም ደግሞ ወደ ታንኳ ገባ፤ ወደ
ማዶም ሄደ። ፲፬እንጀራ መያዝም ረስተው ነበ
ርና በታንኳው ውስጥ ለእነርሱ ከአንዲት እን

---

፩ “ልብስዋንም ለብሳ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፰፥፲፩ ማቴ ፲፪፥፴፰፤ ሉቃ. ፲፩፥፲፮። ፰፥፲፪ ማቴ. ፲፪፥፴፱፤ ሉቃ. ፲፩፥፳፱።

ጀራ በቀር አልነበራቸውም። ፲፭ጌታችንም፥ "ዕወቁ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ" ብሎ አዘዛቸው። ፲፮እነርሱም፥ "እንጀራ አልያዝንምና እንዲህ ይለናል?" ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ። ፲፯ጌታችን ኢየሱስም ዐወቀባቸውና እንዲህ አላቸው፥ "እንጀራ ስለሌላችሁ ለምን ታስባላችሁ? ገና አታውቁምን? ወይስ አታስተውሉምን? ልባችሁስ ደንዝዞአልን? ፲፰ዐይን አላችሁ፥ አታዩምን? ጆሮም አላችሁ፥ አትሰሙምን? ወይስ አታስቡምን? ፲፱አምስቱን እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰዎች በቈረስሁ ጊዜ የተረፈውን ቍርስራሽ የሞላ ስንት ቅርጫት አነሣችሁ?" እነርሱም፥ "ዐሥራ ሁለት" አሉት። ፳እርሱም፥ "ሰባቱን እንጀራስ ለአራት ሺህ ሰው በቈረስሁ ጊዜ የተረፈውን ቍርስራሽ የሞላ ስንት ቅርጫት አነሣችሁ?" አላቸው፤ እነርሱም፥ "ሰባት" አሉት። ፳፩"እንግዲህ የማታስተውሉ ለምንድን ነው?" አላቸው።

በቤተ ሳይዳ የነበረው ዕውር ስለ መዳኑ

፳፪ወደ ቤተ ሳይዳም በደረሱ ጊዜ፥ አንድ ዕውር ሰው ወደ እርሱ አመጡ፤ እንዲዳስሰውም ለመኑት። ፳፫ያንም ዕውር በእጁ ይዞ ከመንደር አወጣው፤ በዐይኑ ላይም እንትፍ ብሎ ዳሰሰውና፥ "ምን ታያለህ?" አለው። ፳፬ተመልክቶም፥ "ሰዎችን እንደ ዛፎች ወዲያና ወዲህ ሲመላለሱ አያለሁ" አለ። ፳፭ዳግመኛም ዐይኑን ዳሰሰውና አጥርቶ አየ፥ ዳነም፤ ብሩህም ሆኖለት ሁሉን ተመለከተ። ፳፮"ወደ መንደር አትግባ፤ በመንደር ውስጥም ለማንም አንዳች አትናገር" ብሎ ወደ ቤቱ ሰደደው።

ጌታችን በቂሣርያ ሐዋርያትን ስለ መጠየቁ
(ማቴ. ፲፮፥፲፫-፳፤ ሉቃ. ፱፥፲፰-፳፩)

፳፯ጌታችን ኢየሱስም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በፊልጶስ ቂሣርያ ወደ አሉ መንደሮች ሄደ፤ በመንገድም፥ "ሰው እኔን ማን ይለኛል?" ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። ፳፰እነርሱም፥ "አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል" አሉት። ፳፱"እናንተሳ ማን ትሉኛላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው፤ ጴጥሮስም፥ "አንተ ክርስቶስ ነህ" ብሎ መለሰለት። ፴እርሱም ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው።

መከራውን ስለ መናገሩ
(ማቴ. ፲፮፥፳፩-፳፰፤ ሉቃ. ፱፥፳፪-፳፯)

፴፩ሽማግሎችና የካህናት አለቆች፥ ጻፎችም የሰውን ልጅ ይነቅፉት ዘንድ ብዙ መከራም ያጸኑበት ዘንድ እንዳለው፥ እንደሚገድሉትና በሦስተኛው ቀንም እንደሚነሣ ያስተምራቸው ጀመር። ፴፪ይህንም ነገር በግልጥ ይነግራቸው ነበረ፤ ጴጥሮስም ቀርቦ ይከለክለው ጀመረ። ፴፫ተመልሶም ወደ ደቀ መዛሙርቱ አየና፥ "የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና አንተ ሰይጣን ከኋላዬ ሂድ" ብሎ ጴጥሮስን ገሠጸው።

ስለሚያገለግሉት ሰዎች

፴፬ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ሕዝቡን ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ "ሊከተለኝ የሚወድ ሰው ራሱን ይካድ፤ ጨክኖም[፩] የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ይከተለኝ። ፴፭ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ያጠፋታል፤ ሰውነቱን ስለ እኔና ስለ ወንጌል የሚያጠፋትም ያገኛታል። ፴፮ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱን ግን ቢያጠፋ ለሰው ምን ይጠቅመዋል? ፴፯ሰው ለነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል? ፴፰በዚች አመንዝራና ኀጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍረውን ሁሉ፥ የሰው ልጅም በአባቱ ክብር ቅዱሳን መላእክትን አስከትሎ በሚመጣበት ጊዜ ያፍርበታል።

ምዕራፍ ፱

፩"እውነት እላችኋለሁ፤ በዚህ ከቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት በኀይል ስትመጣ እስኪያዩአት ድረስ ሞትን የማይቀምሱት አሉ" አላቸው።

በደብረ ታቦር ክብሩን ስለ መግለጡ
(ማቴ. ፲፯፥፩-፲፫፤ ሉቃ. ፱፥፳፰)

፪በስድስተኛውም ቀን[፪] ጌታችን ኢየሱስ ጴጥሮስን ያዕቆብን ዮሐንስን ይዞ ለብቻቸው

፩ "ጨክኖም" የሚለው በግሪኩ የለም።

፪ ግሪኩ "ከስድስት ቀንም በኋላ" ይላል።

፰፥፲፭ ሉቃ. ፲፪፥፩። ፰፥፲፰ ኤር. ፭፥፳፩፤ ሕዝ. ፲፪፥፪፤ ማር. ፬፥፲፪። ፰፥፳፰ ማር. ፮፥፲፬-፲፭፤ ሉቃ. ፱፥ ፯-፰። ፰፥፳፱ ዮሐ. ፮፥፷፰-፷፱። ፰፥፴፬ ማቴ. ፲፥፴፰፤ ሉቃ. ፲፬፥፳፯። ፰፥፴፭ ማቴ. ፲፥፴፱፤ ሉቃ. ፲፯፥፴፫፤ ዮሐ. ፲፪፥፳፭። ፱፥፪-፯ ፪ ጴጥ. ፩፥፲፯-፲፰።

ወደ ረዥም ተራራ አወጣቸው፤ መልኩም በፊ
ታቸው ተለወጠ። ፫ልብሱም አንጸባረቀ፤ ሸማ
አጣቢም በምድር ላይ እንደዚያ ዓይነት አድ
ርጎ ሊያነጻው እስከማይችል እጅግ ነጭ ሆነ።
፬ሙሴና ኤልያስም ከጌታችን ከኢየሱስ ጋር እየ
ተነጋገሩ ታዩአቸው። ፭ጴጥሮስም መልሶ ጌታ
ችን ኢየሱስን፥ "መምህር ሆይ፥ በዚህ መኖር
ለእኛ መልካም ነው፤ ሦስት ዳስም እንሥራ፤
አንዱን ለአንተ፥ አንዱንም ለሙሴ፥ አንዱንም
ለኤልያስ" አለው። ፮ደንግጠው ነበርና የሚናገ
ረውን አያውቅም ነበር። ፯ደመናም መጥቶ ጋረ
ዳቸው፤ ከደመናውም "የምወደው ልጄ ይህ
ነው፤ እርሱን ስሙት" የሚል ቃል መጣ።
፰ከዚህም በኋላ ድንገት ዙሪያውን በተመለከቱ
ጊዜ፥ ከጌታችን ከኢየሱስ ብቻ በቀር ሌላ ከእ
ነርሱ ጋር ያዩት የለም።

፱ከተራራውም ሲወርዱ የሰው ልጅ ከሙታን
ተለይቶ እስኪነሣ ድረስ ጌታችን ኢየሱስ ያዩ
ትን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው። ፲ቃሉንም
ይዘው፥ "ከሙታን ተለይቶ መነሣት ምንድን
ነው?" ብለው እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ።

### ከደቀ መዛሙርቱ ስለ ቀረበው ጥያቄ

፲፩ደቀ መዛሙርቱም፥ "ጻፎች፥ ኤልያስ አስ
ቀድሞ ይመጣ ዘንድ አለው ለምን ይላሉ?"
ብለው ጠየቁት። ፲፪እርሱም መልሶ እንዲህ አላ
ቸው፥ "ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል፤ ሁሉ
ንም ያቀናል፤ እንኪያ ብዙ መከራ እንደሚያጸ
ኑበት፥ እንደሚንቁትም ስለ ሰው ልጅ እንዴት
ተብሎ ተጻፈ? ፲፫ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ኤል
ያስ በእርግጥ መጥቶአል፤ ስለ እርሱ እንደ ተጻ
ፈም የወደዱትን ሁሉ አደረጉበት።"

### ጋኔን ይጥለው የነበረውን ሰው እንደ ፈወሰው
(ማቴ. ፲፯፥፲፬-፳፩፤ ሉቃ. ፱፥፴፯-፵፫)

፲፬ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመጣ ጊዜ፥ ብዙ
ሰዎች ከብበዋቸው፥ ጻፎችም ሲከራከሩአቸው
አገኘ። ፲፭ሰዎችም ሁሉ ባዩት ጊዜ ደነገጡ፤
ወዲያውም ወደ እርሱ ሮጡና እጅ ነሡት።
፲፮ጻፎችንም፥ "ስለምን ትከራከሩአቸዋላችሁ?"
ብሎ ጠየቃቸው። ፲፯ከሕዝቡም መካከል አንድ
ሰው መልሶ እንዲህ አለ፥ "መምህር ሆይ፥
ልጄን ወደ አንተ አምጥቼዋለሁ፤ ዲዳ ጋኔን
ይዞታልና። ፲፰ባገኘበትም ቦታ ይጥለዋል፤ ያፈራ
ግጠዋል፤ አረፋ ያስደፍቀዋል፤ ጥርሱንም ያፋ
ጩዋል፤ ያደርቀዋል፤ ለደቀ መዛሙርትህም
ያወጡለት ዘንድ ነገርኋቸው፤ ነገር ግን መፈ
ወስ ተሳናቸው። ፲፱እርሱም መልሶ፥ "እምነት
የሌላት ትውልድ፥ እስከ መቼ ድረስ ከእናንተ
ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼ ድረስስ እታገሣች
ኋለሁ? ወደዚህ ወደ እኔ አምጡት" አላቸው።
፳ወደ እርሱም ወሰዱት፤ ያም ጋኔን ባየው ጊዜ
ወዲያውኑ በመሬት ላይ ጣለው፤ አፈራገጠው፤
አረፋም አስደፈቀው። ፳፩ጌታችን ኢየሱስም፥
"የያዘው ከመቼ ጀምሮ ነው?" ብሎ አባቱን
ጠየቀው፤ እርሱም፥ "ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው።
፳፪ብዙ ጊዜ ሊገድለው ወደ ገደል[፪] ወደ እሳ
ትም ወደ ውኃም ይጥለዋል፤ ነገር ግን ቢቻልህ
እዘንልኝ፤ ርዳኝም" አለው።[፫] ፳፫ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ "ቢቻልህ ብለሃል፤ ብታምንስ ለሚያ
ምን ሁሉ ይቻላል" አለው። ፳፬የዚያ ብላቴና
አባትም፥ "አቤቱ፥ አምናለሁ፤ ነገር ግን አለ
ማመኔን ርዳው" ብሎ ጮኸ። ፳፭ጌታችን ኢየ
ሱስም ሰው ሲራወጥ አይቶ "አንተ ዲዳ፥ ደን
ቆሮም ጋኔን ከእርሱ እንድትወጣ፥ ዳግመኛም
እንዳትመለስበት እኔ አዝዤሃለሁ" ብሎ ያን
ክፉ ጋኔን ገሠጸው። ፳፮ጮኾም እጅግ አፈራገ
ጠውና ወጣ፤ ብዙዎችም ሞተ እስኪሉ ድረስ
እንደ በድን ሆነ። ፳፯ጌታችን ኢየሱስም በእጁ
ይዞ አስነሣው፥ ቆመም። ፳፰ወደ ቤትም በገቡ
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ሆነው፥ "ስለ
ምን እኛ እርሱን ማውጣት ተሳነን?" አሉት።
፳፱እርሱም፥ "ይህ ወገን ያለ ጾምና[፬] ያለ ጸሎት
ሊወጣ አይችልም" አላቸው።

### ስለሚደርስበት መከራውና ሞቱ
(ማቴ. ፲፯፥፳፪፡፳፫፤ ሉቃ. ፱፥፵፫)

፴ከዚያም ወጥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤
ማንም ያውቀው ዘንድ አልፈቀደም። ፴፩"የሰው
ልጅ በሰዎች እጅ ተላልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው፤
ይገድሉታልም፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል"
ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ያስተምራቸው ነበርና።
፴፪የነገራቸውንም አላስተዋሉም፤ ሊጠይቁትም
ይፈሩ ነበር።

---

፪ ግሪኩ "ወደ ገደል ..." አይልም።

፫ ግሪኩ "እዘንልን ርዳንም" ይላል።

፬ "ጾም" የሚለው በግሪኩ የለም።

፱፥፯ ማቴ. ፫፥፲፯፤ ማር ፩፥፲፩፤ ሉቃ. ፫፥፳፪። ፱፥፲፩ ሚል. ፬-፭፤ ማቴ. ፲፩፥፲፬።

### ትሕትናን ስለ ማስተማሩ

(ማቴ. ፲፰፥፩-፭፤ ሉቃ. ፱፥፵፮-፵፰)

፴፫ወደ ቅፍርናሆም ደርሶ ወደ ቤት በገባ ጊዜ፥ "በመንገድ እርስ በርሳችሁ ምን ትነጋገሩ ነበር?" ብሎ ጠየቃቸው። ፴፬በመንገድ እርስ በርሳቸው፡- "ከእነርሱ ማን ይበልጣል?" ተባብለው ነበርና ዝም አሉ። ፴፭ተቀምጦም ዐሥራ ሁለቱን ጠርቶ፥ "አለቃ ሊሆን የሚወድ ራሱን ለሁሉ ዝቅ ያድርግ፤ ለሁሉም አገልጋይ ይሁን" አላቸው። ፴፮ሕፃንንም ይዞ በመካከላቸው አቆመው፤ አቅፎም እንዲህ አላቸው፡- ፴፯"እንደዚህ ካሉ ሕፃናት አንዱን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝንም እንጂ እኔን ብቻ የሚቀበል አይደለም።"

### አጋንንትን ስለሚያወጣው ሰው

(ሉቃ. ፱፥፵፱-፶)

፴፰ዮሐንስም መልሶ፥ "መምህር ሆይ፥ በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ ያየነው አንድ ሰው አለ፤ ከእኛም ጋር ስላልተከተለህ ከለከልነው" አለው። ፴፱ጌታችን ኢየሱስ ግን እንዲህ አላቸው፥ "በስሜ ተአምራትን የሚያደርግ፥ ወዲያውም በእኔ ላይ ክፉ ቃልን ሊናገር የሚችል የለምና አትከልክሉት። ፵ባላጋራችሁ ካልሆነ ባልንጀራችሁ ነውና።[፳] ፵፩እናንተ የክርስቶስ ስለ ሆናችሁ፥ በስሜ ቀዝቃዛ[፳፩] ጽዋ ውኃ የሚያጠጣችሁ ዋጋውን እንደማያጣ እውነት እላችኋለሁ።

፵፪"በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን የሚያስት አህያ የሚፈጭበት[፳፪] የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢሰጥም ይሻለዋል። ፵፫እጅህም ብታስትህ ቊረጣት፤ ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና። ፵፬ሁለት እጅ ኖሮህ እሳቱ ወደማይጠፋበት፥ ትሉም ወደማያንቀላፋበት ወደ ገሃነም እሳት ከምትገባ፥ ፵፭እግርህም ብታስትህ ቊረጣት፤ አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና። ፵፮ሁለት እግር ኖሮህ እሳቱ ወደማይጠፋበት፥ ትሉም ወደማያንቀላፋበት ወደ ገሃነም እሳት ከምትገባ። ፵፯ዐይንህም ብታስትህ አውጣት፤ አንድ ዐይና ሆነህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ብትገባ ይሻልሃልና። ፵፰ሁለት ዐይን ኖሮህ እሳቱ ወደማይጠፋበት፥ ትሉም ወደማያንቀላፋበት ወደ ገሃነም እሳት ከምትገባ።

### ስለ ፍቅር

፵፱"ሁሉም በእሳት ይጣፍጣልና መሥዋዕት ሁሉ በጨው ይጣፍጣል። ፶ጨው መልካም ነው፤ ጨው ግን አልጫ ቢሆን በምን ታጣፍጡታላችሁ? በውስጣችሁ ጨው ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም ተስማሙ።"

## ምዕራፍ ፲

### ስለ ጋብቻ የተሰጠ ትእዛዝ

(ማቴ. ፲፱፥፩-፲፪፤ ሉቃ. ፲፮፥፲፰)

፩ከዚያም ተነሥቶ በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ይሁዳ ሀገር ሄደ፤ ሕዝቡም ደግሞ ከእርሱ ጋር ሄዱ፤ እንደ አስለመደም ያስተምራቸው ነበር። ፪ፈሪሳውያንም መጥተው፥ "ለሰው ሚስቱን መፍታት ይገባዋልን?" ብለው ሊፈትኑት ጠየቁት። ፫ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ "ሙሴ ምን አዘዛችሁ?" አላቸው። ፬እነርሱም፥ "ሙሴስ የምትፈታበትን ደብዳቤ ጽፎ እንዲፈታት ፈቀደ" አሉት። ፭ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ "ስለ ልባችሁ ክፋት ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ሙሴ ይህን ትእዛዝ ሰጣችሁ። ፮ከፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴትን ፈጠረ። ፯ስለዚህም ወንድ አባትና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላታል። ፰ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ፤ እንግዲያስ አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም። ፱እንግዲህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ።"

---

[፳] ግሪኩ "የማይቃወመን እርሱ ከእኛ ጋር ነውና ..." ይላል።

[፳፩] "ቀዝቃዛ" የሚለው በግሪኩ የለም።

[፳፪] "አህያ የሚፈጭበትን" የሚለው በግሪኩ የለም።

፱፥፴፬ ሉቃ. ፳፪፥፳፬። ፱፥፴፭ ማቴ. ፳፥፳፮-፳፯፤ ፳፫፥፲፩፤ ማር. ፲፥፵፫-፵፬፤ ሉቃ. ፳፪፥፳፮።
፱፥፴፯ ማቴ. ፲፥፵፤ ሉቃ. ፲፥፲፮፤ ዮሐ. ፲፫፥፳። ፱፥፵ ማቴ. ፲፪፥፴፤ ሉቃ. ፲፩፥፳፫። ፱፥፵፩ ማቴ. ፲፥፵፪።
፱፥፵፪ ማቴ. ፲፰፥፮። ፱፥፵፫ ማቴ. ፭፥፴። ፱፥፵፯ ማቴ. ፭፥፳፱። ፱፥፵፰ ኢሳ. ፷፮፥፳፬።
፱፥፶ ማቴ. ፭፥፲፫፤ ሉቃ. ፲፬፥፴፬-፴፭። ፲፥፬ ዘዳ. ፳፬፥ ፩-፬፤ ማቴ. ፭፥፴፩። ፲፥፮ ዘፍ. ፩፥፳፯፤ ፭፥፪።
፲፥፯-፰ ዘፍ. ፪፥፳፬።

፲በቤትም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ
ነገር ጠየቁት። ፲፩እንዲህም አላቸው፤ “ሚስ
ቱን የሚፈታና ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ በእ
ርስዋ ላይ ያመነዝራል። ፲፪እርስዋም ባልዋን
ፈትታ ሌላ ብታገባ ታመነዝራለች።”

### ሕፃናትን ስለ መባረኩ

(ማቴ. ፲፱፥፲፫-፲፭፤ ሉቃ. ፲፰፥፲፭)

፲፫ይባርካቸውም ዘንድ ሕፃናትን አመጡ
ለት፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን
ገሠጹአቸው። ፲፬ጌታችን ኢየሱስ ግን አይቶ
ተቈጣ፤ እንዲህም አላቸው፤ “ሕፃናትን ወደ
እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤
የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት
ናትና። ፲፭እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ
አይገባባትም።” ፲፮አቀፋቸውም፤ እጁንም በራ
ሳቸው ላይ ጭኖ ባረካቸው።

### ስለ ጐልማሳው ባለጸጋ

(ማቴ. ፲፱፥፲፮-፴፤ ሉቃ. ፲፰፥፲፰-፴)

፲፯በመንገድ ሲሄድም አንድ ሰው መጥቶ ሰገ
ደለትና፤ “ቸር መምህር ሆይ፥ የዘለዓለም ሕይ
ወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?” ብሎ ጠየ
ቀው። ፲፰ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለው፥
“ለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብ
ሔር በቀር ቸር የለም። ፲፱ትእዛዛትን ታውቃ
ለህ፤ አታመንዝር፤ አትግደል፤ አትስረቅ፤ በሐ
ሰት አትመስክር፤ አታታልል፤[፩] አባትህንና እና
ትህን አክብር።” ፳እርሱም መልሶ፥ “መም
ህር ሆይ፥ ይህንስ ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሬ ጠብ
ቄአለሁ” አለው። ፳፩ጌታችን ኢየሱስም ወደ
እርሱ ተመልክቶ ወደደው፤ “ፍጹም ልትሆን
ብትወድስ አንዲት ነገር ቀርታሃለች፤ ሂድና
ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለነዳያን ስጥ፤ በሰማያትም
መዝገብ ታገኛለህ፤ የሞትህንም መስቀል ተሸ
ክመህ ና፥ ተከተለኝ” አለው። ፳፪ስለዚህም
ነገር ፊቱ ጠቈረ፤ ብዙ ንብረትም ነበረውና
እያዘነ ሄደ።

፳፫ጌታችን ኢየሱስም ወደ ደቀ መዛሙርቱ
ዘወር ብሎ ተመልክቶ፥ “ገንዘብ ላለው ሰው
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እን
ዴት ጭንቅ ነው?” አላቸው። ፳፬ደቀ መዛሙ
ርቱም ይህን ነገር አደነቁ፤ ዳግመኛም ጌታችን
ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፡-
“ልጆቼ ሆይ፥ በገንዘባቸው ለሚታመኑ ሰዎች
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እን
ዴት ጭንቅ ነው? ፳፭ባለጸጋ ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያ
ልፍ ይቀላል።” ፳፮እነርሱም እጅግ አድንቀው
እርስ በርሳቸው፥ “እንግዲህ ማን ሊድን ይች
ላል?” ተባባሉ። ፳፯ጌታችን ኢየሱስም አያቸ
ውና፥ “በሰው ዘንድ ይህ አይቻልም፤ በእግዚ
አብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል” አላቸው።

### የሚከተሉት ስለሚያገኙት ዋጋ

፳፰ጴጥሮስም፥ “እነሆ፤ እኛ ሁሉን ትተን ተከ
ተልንህ” ይለው ጀመር። ፳፱ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “እውነት እላችኋለሁ፤
ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም እርሻን፥
ወይም ወንድሞችን፥ ወይም እኅቶችን፥ ወይም
አባትን፥ ወይም እናትን፥ ወይም ሚስትን፥
ወይም ልጆችን የሚተው፥ በዚህ ዓለም በመከ
ራና በስደት መቶ እጥፍ ቤትንና እርሻን፥ ወንድ
ሞችንና እኅቶችን፥ አባትንና እናትን፥ ልጆችንም
የማያገኝ የለም። ፴በሚመጣውም ዓለም የዘለዓለም
ሕይወትን ያገኛል። ፴፩ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞችን
ይሆናሉ፤ ኋለኞችም ፊተኞችን ይሆናሉ።”

### ስለ መከራዉ፥ ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤዉ

(ማቴ. ፳፥፲፯-፲፱፤ ሉቃ. ፲፰፥፴፩)

፴፪በመንገድም ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጡ ጌታ
ችን ኢየሱስ ይቀድማቸው ነበርና ተደነቁ፤ የሚ
ከተሉትም ፈሩ፤ ዐሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ
ወስዶ ይደርስበት ዘንድ ያለውን ይነግራቸው
ጀመር። ፴፫እንዲህም አላቸው፥ “እነሆ፥ ወደ ኢየ
ሩሳሌም እንወጣለን፥ የካህናት አለቆችና ጻፎችም
የሰውን ልጅ ይይዙታል፤ የሞት ፍርድም ይፈር
ዱበታል፤ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል።
፴፬ያፌዙበታል፤ ይተፉበታልም፤ ይገርፉታልም፤
ይገድሉታልም፤ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል።”

### ስለ ዘብዴዎስ ልጆች ጥያቄ

(ማቴ. ፳፥፳-፳፰)

፴፭ሁለቱ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐ
ንስም ወደ እርሱ ቀርበው፥ “መምህር ሆይ፥

---

፩ ግእዙ “አትቀማ” ይላል።

፲፥፲፩-፲፪ ማቴ. ፭፥፴፪፤ ፩ቆሮ. ፯፥፲-፲፩። ፲፥፲፭ ማቴ. ፲፰፥፫። ፲፥፲፱ ዘፀ. ፳፥፲፪-፲፮፤ ዘዳ. ፭፥ ፲፮-፳።
፲፥፴፩ ማቴ. ፳፥፲፮።

የምንለምንህን እንድታደርግልን እንሻለን”
አሉት። ፴፮እርሱም፥ “ምን ላደርግላችሁ ትሻ
ላችሁ?” አላቸው። ፴፯እነርሱም፥ “በጌትነትህ
አንዳችን በቀኝህ፥ አንዳችንም በግራህ እንድን
ቀመጥ ፍቀድልን” አሉት። ፴፰ጌታችን ኢየሱ
ስም እንዲህ አላቸው፥ “የምትለምኑትን አታ
ውቁም፤ እኔ የምጠጣውን ጽዋዕ ልትጠጡ
ትችላላችሁን? እኔ የምጠመቀውን ጥምቀትስ
ትጠመቃላችሁን?” ፴፱እነርሱም፥ “አዎን፥ እን
ችላለን” አሉት፤ ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
አላቸው፥ “እኔ የምጠጣውንስ ጽዋዕ ትጠጣላ
ችሁ፤ እኔ የምጠመቃትን ጥምቀትም ትጠመቃ
ላችሁ። ፵በቀኜና በግራዬ መቀመጥን ግን ሰማ
ያዊ አባቴ[፪] ለሌሎች አዘጋጅቶላቸዋል እንጂ
እኔ የምሰጣችሁ አይደለም።” ፵፩ዐሥሩም ሰም
ተው በሁለቱ ወንድማማቾች[፫] በያዕቆብና በዮሐ
ንስ ተቈጡ። ፵፪ጌታችን ኢየሱስም ወደ እርሱ
ጠርቶ እንዲህ አላቸው፥ “አሕዛብን አለቆቻ
ቸው እንዲፈርዱባቸው፥ ታላላቆቻቸውም እን
ዲሠለጥኑባቸው አታውቁምን? ፵፫ለእናንተስ
እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ከእናንተ አለቃ
ሊሆን የሚወድ አገልጋይ ይሁናችሁ። ፵፬ከእ
ናንተም ታላቅ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ታዛዥ
ይሁናችሁ። ፵፭የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን
ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ ሊያገለግሉት አል
መጣምና።”

### ስለ ዕውሩ ስለ ጤሜዎስ ልጅ መዳን

(ማቴ. ፳፥፳፱-፴፬፤ ሉቃ. ፲፰፥፴፭-፵፫)

፵፮ወደ ኢያሪኮም ገባ፤ ከኢያሪኮም በወጣ
ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ነበሩ፤
ብዙ ሰውም ነበረ፤ የጤሜዎስ ልጅ ዕውሩ
በርጤሜዎስም በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለ
ምን ነበር። ፵፯የናዝሬቱ ኢየሱስ እንደ ሆነም
ሰምቶ፥ “የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ማረኝ”
ብሎ ጮኸ። ፵፰ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠ
ጹት፤ እርሱ ግን ድምፁን ከፍ አደረገና፥
“የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረኝ” አለ። ፵፱ጌታችን
ኢየሱስም ቆመና፥ “ጥሩት” አለ፤ እነርሱም
ዕውሩን ጠሩት፤ “በርታና ተነሥ፥ መምህር
ይጠራሃል” አሉት። ፶እርሱም ተነሥቶ ልብ
ሱን ትቶ[፬] ወደ ጌታችን ኢየሱስ መጣ። ፶፩ጌታ
ችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ምን ላደርግልህ ትሻ
ለህ?” አለው፤ ዕውሩም፥ “መምህር ሆይ፥
እንዳይ ነው” አለው። ፶፪ጌታችን ኢየሱስም፥
“ሂድ፤ እምነትህ አዳነችህ” አለው፤ ወዲያ
ውም አየ፤ በመንገድም ተከተለው።

## ምዕራፍ ፲፩

### በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መግባቱ

(ማቴ. ፳፩፥፩-፲፩፤ ዮሐ. ፲፪፥፲፪-፲፱)

፩ኢየሩሳሌም ለመግባት በደብረ ዘይት አጠ
ገብ ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በደረሱ
ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ። ፪እንዲ
ህም አላቸው፥ “በፊታችሁ ወዳለችው መን
ደር ሂዱ፤ ወደ መንደርም በገባችሁ ጊዜ፥
ሰው በላዩ ያልተቀመጠበት የአህያ ውርንጫ
ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ፍቱና አምጡልኝ።
፫‘ምን ታደርጋላችሁ?’ የሚላችሁ ሰው ቢኖ
ርም ‘ጌታው ይሻዋል’ በሉ፤ ወዲያውኑም
ወደዚህ ይሰድደዋል።” ፬ሄደውም በበሩ አጠ
ገብ ባለው ሜዳ በመንገድ ዳር የታሰረ ውር
ንጫ አገኙ፤ ፈቱትም። ፭ከዚያ ቆመው የነ
በሩትም፥ “ምን ልታደርጉት ነው ውርንጫ
ዉን የምትፈቱት?” አሉአቸው። ፮ጌታችን
ኢየሱስ እንደ አዘዛቸውም ነገሩአቸው፤ እነ
ርሱም ተዉአቸው። ፯ውርንጫዉንም ወደ
ጌታችን ኢየሱስ ወሰዱና ልብሳቸውን በላዩ
ደልድለው አስቀመጡት። ፰ብዙዎችም ልብ
ሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎችም
ከዛፍ ቅጠሎችን እየቈረጡ ያነጥፉ ነበር።
፱በፊት የሚሄዱ፥ በኋላም የሚከተሉ እንዲህ
እያሉ ይጮኹ ነበር፥ “ሆሣዕና፥ በእግዚአብ
ሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው። ፲በእግዚአ
ብሔር ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት
መንግሥት የተባረከች ናት፤ ሆሣዕና በአር
ያም።” ፲፩ጌታችን ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳ
ሌም ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፤ ሁሉንም ተመ
ልክቶ በመሸ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ ጋር ወደ
ቢታንያ ሄደ።

---

፪ “ሰማያዊ አባቴ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፫ “በሁለቱ ወንድማማቾች” የሚለው በግእዙ ብቻ።

፬ በአንዳንድ የግእዝ ዘርዕ “ልብሱን ትቶ” በማለት ፋንታ “ልብሱን ለብሶ” የሚል ይገኛል።

፲፥፴፰ ሉቃ. ፲፪፥፶። ፲፥፵፪-፵፫ ሉቃ. ፳፪፥፳፭-፳፯። ፲፥፵፫-፵፬ ማቴ. ፳፫፥፲፩፤ ማር ፱፥፴፭፤ ሉቃ. ፳፪፥፳፮።
፲፩፥፱ መዝ. ፻፲፰፥፳፭-፳፯።

### ስለ ተረገመችው በለስ
(ማቴ. ፳፩፥፲፰-፲፱)

፲፪በነጋዉም ከቢታንያ በወጣ ጊዜ ተራበ።
፲፫በለስንም ከሩቅ አየ፤ ቅጠልም ነበራት፤ በው
ስጥዋም የሚያገኘው ፍሬ እንዳለ ሊያይ ሄደ፤
ወደ እርስዋም በሄደ ጊዜ ከቅጠል ብቻ በቀር
ምንም አላገኘባትም፤ የበለስ ጊዜ አልነበረ
ምና። ፲፬መልሶም፥ "ከእንግዲህ ወዲህ ለዘለዓ
ለም ከአንቺ ፍሬ የሚበላ አይኑር" አላት፤ ደቀ
መዛሙርቱም ሰሙት።

### ቤተ መቅደስን ስለሚያረክሱ
(ማቴ. ፳፩፥፲፪-፲፯፤ ሉቃ. ፲፱፥፵፭)

፲፭ወደ ኢየሩሳሌምም በደረሱ ጊዜ ወደ ቤተ
መቅደስ ገባ፤ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚለ
ውጡትን ያባርር ጀመር፤ የገንዘብ ለዋፄች
ንም መደርደሪያ፥ የርግብ ሻጮችንም ወንበር
ገለበጠ። ፲፮ማንም ዕቃ ተሸክሞ በመቅደስ እን
ዲያልፍ አልፈቀደም። ፲፯"ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ
የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎ የለምን?
እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት"
ብሎ አስተማራቸው። ፲፰የካህናት አለቆችና ጻፎ
ችም ሰምተው የሚገድሉበትን ምክንያት ፈለጉ፤
ነገር ግን ሕዝቡ ሁሉ ትምህርቱን ያደንቁ ነበ
ርና ፈሩት። ፲፱በመሸም ጊዜ ከከተማ ወደ ውጭ
ወጣ። ፳በነጋዉም በተመለሱ ጊዜ ያቺን በለስ
ከስርዋ ደርቃ አገኙአት። ፳፩ጴጥሮስም ትዝ አለ
ውና፥ "መምህር ሆይ፥ እነሆ፥ ያቺ የረገም
ሃት በለስ ደርቃለች" አለው። ፳፪ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ "እግዚአብሔ
ርን ማመን ይኑራችሁ፤ ፳፫እውነት እላችኋለሁ፥
ይህን ተራራ ተነሥተህ ወደ ባሕር ተወርወር
ብትሉት፥ በልባችሁም ባትጠራጠሩ፥ ብታም
ኑም እንደ ተናገራችሁት ይሆናል። ፳፬ስለዚህ እላ
ችኋለሁ፥ "አምናችሁ የምትጸልዩትንና የምትለ
ምኑትንም ሁሉ ታገኙላችሁ፤ ይሆንላችሁማል።

### በደልን ይቅር ስለ ማለት

፳፭"በምትጸልዩበትም ጊዜ በሰማያት ያለው
አባታችሁ በደላችሁን ይቅር እንዲላችሁ በወን
ድማችሁ ያለውን በደል ይቅር በሉ። ፳፮እናንተ
ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም
በደላችሁን ይቅር አይላችሁም።"

### ስለ ሥልጣኑ የቀረበ ጥያቄ
(ማቴ. ፳፩፥፳፫-፳፯፤ ሉቃ. ፳፥፩-፰)

፳፯ዳግመኛም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፤ በቤተ
መቅደስም ሲመላለስ የካህናት አለቆችና ጻፎች
ሽማግሌዎችም ወደ እርሱ መጡ። ፳፰"በማን
ሥልጣን ይህን ታደርጋለህ? ወይስ ይህን ለማ
ድረግ ይህን ሥልጣን ማን ሰጠህ?" አሉት።
፳፱ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ "እኔም
አንዲት ነገርን እጠይቃችኋለሁ፤ ንገሩኝ፤ እኔም
በማን ሥልጣን ይህን እንደማደርግ እነግራችኋ
ለሁ። ፴የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ነበረች? ከሰ
ማይ ነበረችን? ወይስ ከሰው? ንገሩኝ።" ፴፩እርስ
በርሳቸውም እንዲህ ተባባሉ፥ "ከሰማይ ነው
ብንለው እንኪያ ለምን አላመናችሁበትም? ይለ
ናል። ፴፪ከሰው ነው ብንለውም ሕዝቡን እንፈ
ራለን፤" ሁሉ ዮሐንስን በእውነት እንደ ነቢይ
ያዩት ነበርና። ፴፫መልሰውም ለጌታችን ኢየ
ሱስ፥ "አናውቅም" አሉት፤ ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ፥ "እኔም በማን ሥልጣን ይህን እንደማደ
ርግ አልነግራችሁም" አላቸው።

## ምዕራፍ ፲፪

### ስለ ወይኑ ቦታ ምሳሌ
(ማቴ. ፳፩፥፴፫-፵፯፤ ሉቃ. ፳፥፱-፲፱)

፩ምሳሌም ይመስልላቸው ጀመረ፤ እንዲ
ህም አላቸው፥ "አንድ ሰው የወይን አትክልት
ተከለ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፤ መጥመቂያም አስ
ቈፈረለት፤ በውስጡም ግንብ ሠራ፥ ለገባሮችም
ሰጥቶ ወደ ሌላ ሀገር ሄደ። ፪በጊዜውም ከወ
ይኑ ፍሬ ያመጣለት ዘንድ ወደ ገባሮች አገልጋ
ዩን ላከ። ፫ይዘውም ገረፉት፤ ባዶ እጁንም ሰደ
ዱት። ፬ዳግመኛም ሌላዉን አገልጋዩን ወደ እነ
ርሱ ላከ፤ እርሱንም ደበደቡት፤ ቀጥቅጠውና
አዋርደውም ሰደዱት። ፭እንደገናም ሌላዉን አገ
ልጋዩን ላከ፤ እርሱንም ገደሉት፤ ሌሎችንም
ብዙዎች አገልጋዮችን ላከ፤ የገረፉትም አለ፤
የገደሉትም አለ። ፮የሚወደውም አንድ ልጅ ነበ
ረው፤ ከሁሉም በኋላ 'ልጄንስ ያፍሩታል' ብሎ
ወደ እነርሱ ላከው። ፯ገባሮችም:- 'ወራሹ ይህ
ነው፤ ኑ፤ እንግደለውና ርስቱን እጅ እናድርግ'
አሉ። ፰ይዘውም ከወይኑ ቦታ ወደ ውጭ አው
ጥተው ገደሉት።፩ ፱እንግዲህ የወይኑ ባለቤት

---

፩ ግሪኩ "ይዘውም ገደሉት ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ ጣሉት" ይላል።

፲፩፥፲፯ ኢሳ. ፶፮፥፯፤ ኤር. ፯፥፲፩። ፲፩፥፳፫ ማቴ. ፲፯፥፳፤ ፩ቆሮ. ፲፫፥፪። ፲፩፥፳፭-፳፮ ማቴ. ፮፥፲፬-፲፭።

ምን ያደርጋቸው ይሆን? መጥቶ እነዚያን ገባ
ሮች ያጠፋቸዋል፤ ወይኑንም ለሌሎች ይሰጣል።
፲ይህንስ በመጽሐፍ አላነበባችሁምን? ‘ግንበኞች
የናቁአት ድንጋይ እርስዋ የማዕዘን ራስ ሆነች።
፲፩እርስዋ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፤ ለዐይኖ
ቻችንም ድንቅ ናት’።”
፲፪ይህንም ምሳሌ ስለ እነርሱ እንደ ተናገረ
ዐውቀዋልና ሊይዙት ወደዱ፤ ነገር ግን ሕዝ
ቡን ፈሩ፤ ትተውትም ሄዱ።

### ለቄሳር ግብር ስለ መክፈል የቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፳፪፥፲፭-፳፪፤ ሉቃ. ፳፥፳)

፲፫ፈሪሳውያንም በቃሉ ያስቱት ዘንድ ሰዎ
ችን ከሄሮድስ ሰዎች ጋር ወደ እርሱ ላኩ።
፲፬እነርሱም መጥተው እንዲህ አሉት፤ “መም
ህር ሆይ፥ አንተ እውነተኛ እንደ ሆንህ እናው
ቃለን፤ ማንም አያሳዝንህም፤ የሰው ፊትም
አይተህ አታዳላም፤ በእውነት የእግዚአብሔ
ርን መንገድ ታስተምራለህና ለቄሣር ግብር
መስጠት ይገባልን? ወይስ አይገባም? እንስ
ጥን? ወይስ አንስጥ?” ፲፭ጌታችን ኢየሱስም
ተንኰላቸውን ዐወቀባቸውና፥ “ለምን ትፈት
ኑኛላችሁ? ገንዘቡን አምጥታችሁ አሳዩኝ” አላ
ቸው። ፲፮እነርሱም አመጡለት፤ “ይህ መልኩ፥
ጽሕፈቱስ የማን ነው?” አላቸው፤ እነርሱም
“የቄሣር ነው” አሉት። ፲፯ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ፥ “የቄሣርን ለቄሣር ስጡ፤ የእግዚአብ
ሔርንም ለእግዚአብሔር አድርጉ” አላቸው፤
አደነቁትም።

### ትንሣኤ ሙታን የለም ከሚሉ ወገኖች የቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፳፪፥፳፫-፴፫፤ ሉቃ. ፳፥፳፯-፵)

፲፰ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃው
ያን ወደ እርሱ መጡ። ፲፱እንዲህም ብለው ጠየ
ቁት፥ “መምህር ሆይ፥ የአንድ ሰው ወንድም
ልጅ ሳይኖረው ሚስቱን ትቶ ቢሞት ወንድሙ
ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ
ሙሴ ጽፎልን ነበር። ፳እንግዲህ በእኛ ዘንድ
ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፤ ታላቁ ሚስት አግ
ብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ። ፳፩ሁለተኛዉም
አገባትና ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤ ሦስተኛዉም
እንዲሁ። ፳፪ሰባቱም አገቡአት፤ ዘርም አልተ
ዉም፤ ከሁሉም በኋላ ያቺ ሴት ሞተች። ፳፫እን
ግዲህ ሙታን በሚነሡበት ጊዜ ከእነርሱ ለማ
ንኛው ሚስት ትሆናለች? ሰባቱም አግብተ
ዋት ነበርና።” ፳፬ጌታችን ኢየሱስም መልሶ
እንዲህ አላቸው፥ “መጻሕፍትንና የእግዚአብ
ሔርን ኀይል ባለማወቅ ተሳሳታችሁ። ፳፭ሙታ
ንስ በሚነሡበት ጊዜ እነርሱ በሰማያት እንደ
እግዚአብሔር መላእክት ሆነው ይኖራሉ እንጂ
አያገቡም፤ አይጋቡምም። ፳፮ሙታን እንዲነሡ
ግን እግዚአብሔር በዕፀ ጳጦስ ዘንድ ‘እኔ እግ
ዚአብሔር የአንተ አምላክ፥ የአብርሃም አም
ላክ፥ የይስሐቅም አምላክ፥ የያዕቆብም አምላክ
ነኝ’ ብሎ የነገረውን በሙሴ መጽሐፍ አላነበ
ባችሁምን? ፳፯እንግዲህ የሕያዋን አምላክ ነው
እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም፤ እናንተ ግን
በብዙ ትሳሳታላችሁ።”

### ከአንድ ጸሓፊ ስለ ቀረበ ጥያቄ

(ማቴ. ፳፪፥፴፬-፵፤ ሉቃ. ፲፥፳፭-፳፰)

፳፰ከጸሓፊዎችም አንዱ፡- መጥቶ ሲከራከሩ
ሰማና መልካም እንደ መለሰላቸው አይቶ፥
“ከሁሉ የምትበልጠው ትእዛዝ የትኛይቱ
ናት?” ብሎ ጠየቀው። ፳፱ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ እንዲህ አለው፥ “ከትእዛዛቱ ሁሉ የም
ትበልጠው ይህች ናት፤ ‘እስራኤል ሆይ፥
ስማ፤ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ እግዚአ
ብሔር ነው። ፴እግዚአብሔር አምላክህን በፍ
ጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ዐሳ
ብህ፥ በፍጹም ኀይልህ ውደደው፤’ የመጀመ
ሪያይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ፴፩የምትመስላ
ትም ሁለተኛይቱ ይህቺ ናት፤ ‘ወንድምህን
እንደ ራስህ ውደድ’ ከእነዚህ ከሁለቱ ትእ
ዛዛት የሚበልጥ የለም።” ፴፪ያም ጸሓፊ እን
ዲህ አለው፥ “መምህር ሆይ፥ በእውነት መል
ካም ብለሃል፤ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ከእር
ሱም በቀር ሌላ የለም። ፴፫በፍጹም ልብህ በፍ
ጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ዐሳብህ፥ በፍጹም ኀይ
ልህም እርሱን መውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ
ራስ መውደድ ከመባና ከመሥዋዕት ሁሉ ይበ
ልጣል።” ፴፬ጌታችን ኢየሱስም ብልህ እንደ
ሆነ አይቶ “አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት
የራቅህ አይደለህም” አለው፤ ከዚህ በኋላ ግን
ሊጠይቀው የደፈረ የለም።

---

፲፪፥፲-፲፩ መዝ. ፻፲፯፥ ፳፪-፳፫። ፲፪፥፲፰ ሐ.ሥ. ፳፫፥፰። ፲፪፥፲፱ ዘዳ. ፳፭፥፭። ፲፪፥፳፮ ዘፀ. ፫፥፮።
፲፪፥፳፰-፴፬ ሉቃ. ፲፥፳፭-፳፰። ፲፪፥፳፱-፴ ዘዳ. ፮፥ ፬-፭። ፲፪፥፴፩ ዘሌ. ፲፱፥፲፰። ፲፪፥፴፪ ዘዳ. ፬፥፴፭።
፲፪፥፴፫ ሆሴዕ ፮፥፮።

## ጌታችን ኢየሱስ ስለ ጠየቃቸው ጥያቄ

(ማቴ. ፳፪፥፵፩-፵፮፤ ሉቃ. ፳፥፵፩)

፴፭ ጌታችን ኢየሱስም በቤተ መቅደስ ሲያ
ስተምራቸው እንዲህ አላቸው፥ “ጸሓፊ
ዎች፡- ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት
ይላሉ? ፴፮ እርሱ ራሱ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ
‘ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ከእግርህ ጫማ
በታች እስካደርጋቸው ድረስ በቀኜ ተቀ
መጥ አለው’ ይላል። ፴፯ እንግዲህ፤ እርሱ
ራሱ ዳዊት ጌታዬ ያለው እንዴት ልጁ ይሆ
ናል?” ሕዝቡም ሁሉ ደስ ብሎአቸው ያዳ
ምጡት ነበር።

## ከጸሓፊዎች ግብር ስለ መጠበቅ

(ማቴ. ፳፫፥፩-፴፮፤ ሉቃ. ፳፥፵፭)

፴፰ ሲያስተምራቸውም እንዲህ አላቸው፥
“ዕወቁ፤ ረጅም ልብስ ለብሰው ወዲያና
ወዲህ መመላለስን፥ በገባያም እጅ እንዲ
ነሷቸው ከሚወዱ፥ ፴፱ በምኵራብም፥ ፊት
ለፊት መቀመጥን፥ በማዕድም በላይ መቀመ
ጥን ከሚወዱ ከጸሓፊዎች ተጠበቁ። ፵ በረ
ዥም ጸሎታቸው እያመካኙ የመበለቶችን
ገንዘብ የሚበሉ እነዚህ ጽኑ ፍርድን ይቀ
በላሉ።”

## ስለ ሁለት መሐለቅ

(ሉቃ. ፳፩፥፩-፬)

፵፩ ጌታችን ኢየሱስም በሙዳየ ምጽዋት ፊት
ለፊት ተቀምጦ፥ በሙዳየ ምጽዋቱ ገንዘብ
የሚጨምሩ ሰዎችን ያይ ነበር፤ ብዙ ባለጸጎ
ችም ብዙ ገንዘብ ይጨምሩ ነበር። ፵፪ አንዲት
ድሃ መበለትም መጥታ ቆንደራጢስ የሚሉትን
ሁለት መሐለቅ አገባች። ፵፫ ደቀ መዛሙርቱንም
ጠርቶ እንዲህ አላቸው፥ “እውነት እላችኋለሁ
በሙዳየ ምጽዋቱ ውስጥ ገንዘብ ካገቡት ሁሉ
ይህች ደሃ መበለት አብዝታ አገባች። ፵፬ ያገቡ
ሁሉ ከትርፋቸው አግብተዋልና፤ እርስዋ ግን
ከድህነቷ የነበራትን ንብረቷን ሁሉ አግብታ
ለችና።”

# ምዕራፍ ፲፫

## ስለ ቤተ መቅደስ መፍረስና ስለ ዓለም ፍጻሜ

(ማቴ. ፳፬፥፩-፪፤ ሉቃ. ፳፩፥፭፡፮)

፩ ከቤተ መቅደስም በወጣ ጊዜ ከደቀ መዛ
ሙርቱ አንዱ፥ “መምህር ሆይ፥ ድንጋዩና
ሕንጻዉ ምን እንደሚመስል እይ” አለው።
፪ ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “ይህን ታላቅ
ሕንጻ ታያለህን? ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈ
ርስ በዚያ አይቀርም” አለው። ፫ በቤተ መቅደ
ስም ትይዩ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ጴጥ
ሮስና ያዕቆብ፥ ዮሐንስና እንድርያስም ለብቻ
ቸው ጠየቁት። ፬ እንዲህም አሉት፥ “ንገረን
ይህ መቼ ይሆናል? ይህ ሁሉስ በሚደረግበት
ጊዜ ምልክቱ ምንድን ነው?” ፭ ጌታችን ኢየሱ
ስም መልሶ እንዲህ ይላቸው ጀመረ፥ “እንዳያ
ስቱአችሁ ተጠንቀቁ። ፮ ብዙዎች፡- ‘እኔ ክርስ
ቶስ ነኝ’ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎች
ንም ያስቱአቸዋልና። ፯ ጦርነትንና የጦርነትንም
ወሬ በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ ይሆን
ዘንድ አለውና፤ ነገር ግን ፍጻሜው ገና ነው።
፰ ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግ
ሥት ላይ ይነሣል፤ በየቦታዉም የምድር መና
ወጥ ይሆናል፤ ረኃብም ይመጣል፤ ይህ የፃ
ዕር መጀመሪያ ነው። ፱ እናንተ ግን ለራሳችሁ
ተጠንቀቁ፤ ምስክር ሊሆንባቸው ወደ አደባ
ባይ ይወስዱአችኋል፤ በየምኵራቡም ይገርፉአ
ችኋል፤ ስለ እኔም ወደ አለቆች፥ ወደ ነገሥታ
ትም ያደርሱአችኋል። ፲ ለአሕዛብም ሁሉ አስ
ቀድሞ ወንጌል ሊሰበክ ይገባል። ፲፩ ወስደውም
አሳልፈው በሚሰጧችሁ ጊዜ ምን እንደምትና
ገሩ አስቀድማችሁ አትጨነቁ፤ ነገር ግን ያን
ጊዜ የሚሰጣችሁን ተናገሩ፤ መንፈስ ቅዱስ
ነው እንጂ እናንተ የምትናገሩ አይደላችሁምና።
፲፪ ወንድም ወንድሙን፥ አባትም ልጁን ለሞት
አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ
ይነሣሉ፤ ይገድሉአቸዋልም። ፲፫ ስለ ስሜ በሰው
ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ
ፍጻሜ የሚታገሥ ግን እርሱ ይድናል።
፲፬ “ነገር ግን በነቢዩ በዳንኤል የተነገረውን
የጥፋት ርኵሰት በማይገባው በቅዱስ[፩] ቦታ

---

፩ “በቅዱስ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፪፥፴፮ መዝ. ፻፲፥፩። ፲፫፥፱-፲፩ ማቴ ፲፥፲፯-፳። ፲፫፥፲፫ ማቴ. ፲፥፳፪።
፲፫፥፲፬ ዳን. ፱፥፳፯፤ ፲፩፥፴፩፤ ፲፪፥፲፩።

ላይ ቆሞ በአያችሁ ጊዜ የሚያነብበው ያስተ
ውል፤ ያንጊዜም በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች
ይሽሹ። ፲፭በሰገነት ላይ ያለም ወደ ምድር ቤት
አይውረድ፤ በቤቱ ውስጥ ያለውንም ይወስድ
ዘንድ አይግባ። ፲፮በዱር ያለም ልብሱን ይወስድ
ዘንድ ወደ ኋላዉ አይመለስ። ፲፯ነገር ግን በዚያ
ወራት ለፀነሱና ለሚያጠቡ ወዮላቸው። ፲፰ነገር
ግን ሽሽታችሁ በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ።
፲፱በዚያ ወራት እግዚአብሔር ዓለሙን ከፈጠ
ረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ እንደ እርሱ ያል
ሆነ፥ እንግዲህም ደግሞ የማይሆን ጽኑ መከራ
ይሆናልና። ፳እግዚአብሔር እነዚያን ቀኖች ባያ
ሳጥራቸው ኖሮ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም
ነበር፤ ነገር ግን፥ እግዚአብሔር ስለ መረጣ
ቸው ሰዎች እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ። ፳፩ያንጊዜ
'ክርስቶስ በዚህ አለ፤ ወይም በዚያ ነው' የሚ
ላችሁ ቢኖር አትመኑ። ፳፪ሐሰተኞች መሢሖ
ችና ሐሰተኞች ነቢያት ይመጣሉና፤ ለማሳትም
ተአምራትንና ድንቅ ሥራን ያደርጋሉና፤ ቢቻ
ላቸውስ የተመረጡትንም ባሳቱአቸው ነበር።
፳፫እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ ሁሉን አስቀ
ድሜ ነግሬአችኋለሁ።

### ስለ ሰው ልጅ መምጣት

(ማቴ. ፳፬፥፳፱-፴፩፤ ሉቃ. ፳፩፥፳፭-፳፰)

፳፬"ነገር ግን ያንጊዜ ከዚህ ሁሉ መከራ ጋር
ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ብርሃኑን አይሰ
ጥም። ፳፭ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰ
ማያትም ኀይላት ይናወጣሉ። ፳፮ያንጊዜም የሰ
ውን ልጅ በብዙ ኀይልና ክብር በደመና ሲመጣ
ያዩታል። ፳፯ያንጊዜም መላእክትን ይልካቸዋል፤
የተመረጡትንም ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ
ዳርቻ ከአራቱ ማዕዘን ይሰበስቡአቸዋል። ፳፰ምሳ
ሌውንም ከበለስ ዕወቁ፤ ጫፍዋ የለመለመ፥ ቅጠ
ልዋም ያቈጠቈጠ እንደ ሆነ ያንጊዜ መከር እንደ
ደረሰ ታውቃላችሁ። ፳፱እንዲሁ እናንተም ይህን
ሁሉ እንደ ሆነ ባያችሁ ጊዜ፤ ከደጃፍ እንደ
ደረሰ ዕወቁ። ፴እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ
ሳይደረግ ይህቺ ትውልድ አታልፍም። ፴፩ሰማይና
ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።

### ስለ ዕለቲቱና ስለ ሰዓቲቱ

(ማቴ. ፳፬፥፴፮-፵፬)

፴፪"ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት
ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፥ ወልድም
ቢሆን ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም። ፴፫ጊዜዉ
መቼ እንደሚሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤
ትጉ፥ ጸልዩም። ፴፬ቤቱን ትቶ ለአገልጋዮቹም፪
ከእነርሱ ለእያንዳንዳቸው ሥራቸውን ሰጥቶ
በረኛውንም እንዲተጋ አዝዞ ወደ ሩቅ ሀገር
እንደሚሄድ ሰው ነውና። ፴፭እንግዲህ ባለቤቱ
መቼ እንደሚመጣ፥ በማታ፥ ወይም በመንፈቀ
ሌሊት፥ ወይም ዶሮ ሲጮኽ፥ ወይም በማ
ለዳ እንደ ሆነ አታውቁምና፥ ፴፮ድንገት እን
ዳይመጣባችሁ፥ ተኝታችሁም እንዳያገኛችሁ፥
ትጉ፤ ፴፯እነሆ፥ ለእናንተ የምናገረውን ለሁሉ
እላለሁ ትጉ።"

## ምዕራፍ ፲፬

### ስለ ሊቃነ ካህናት ምክር

(ማቴ. ፳፮፥፩-፭፤ ዮሐ. ፲፩፥፵፭-፶፫)

፩ከሁለት ቀንም በኋላ ፋሲካና የቂጣ በዓል
ነበረ፤ የካህናት አለቆችና ጸሐፊዎችም ሊተናኰ
ሉት፥ ሊይዙትና ሊገድሉት ይሹ ነበር። ፪ሕዝ
ቡም እንዳይታወኩ "በበዓል አይሁን" አሉ።

### ጌታችንን ሽቱ ስለ ቀባችው ሴት

(ማቴ. ፳፮፥፮-፲፫፤ ዮሐ. ፲፪፥፩-፰)

፫እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን
ቤት በማዕድ ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋዉ
የከበረ ጥሩ የናርዶስ ሽቱ የሞላበት የአልባ
ስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ መጣች፤ ብልቃጡንም
ከፍታ፩ በራሱ ላይ አፈሰሰችው። ፬እንዲህም
ብለው የተቈጡ ነበሩ፥ "የዚህ ሽቱ ጥፋት
ይህን ያህል ለምንድን ነው? ፭ይህ ሽቱ ከሦ
ስት መቶ ዲናር በላይ ተሽጦ ለነዳያን ሊሰጥ
ባልተቻለም ነበር?" እርስዋንም ገሠጹአት።
፮ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ "ሴቲ
ቱን ተዉአት፤ አታድክሙአትም፤ ለእኔ መል

---

፪ ግሪኩ "ለአገልጋዮቹም ሥልጣንን ሰጥቶ ..." የሚል ይጨምራል።

፩ ግሪኩ "ሰብራ" ይላል።

፲፫፥፲፭-፲፮ ሉቃ. ፲፯፥፴፩። ፲፫፥፲፱ ዳን. ፲፪፥፩፤ ራእ. ፯፥፲፬።

፲፫፥፳፬ ኢሳ. ፲፫፥፲፤ ሕዝ. ፴፪፥፯፤ ኢዩ. ፪፥፲፤ ፴፩፤ ፫፥፲፭፤ ራእ. ፮፥፲፪።

፲፫፥፳፭ ኢሳ. ፴፬፥፬፤ ኢዩ. ፪፥፲፤ ራእ. ፮፥፲፫። ፲፫፥፳፮ ዳን. ፯፥፲፫፤ ራእ. ፩፥፯። ፲፫፥፴፪ ማቴ. ፳፬፥፴፮።

፲፫፥፴፬ ሉቃ. ፲፪፥፴፮-፴፰። ፲፬፥፩ ዘፀ. ፲፪፥፩-፳፯። ፲፬፥፫ ሉቃ. ፯፥፴፯-፴፰።

ካም ሥራ ሠርታለች። ፯ነዳያንንስ ዘወትር በእ
ናንተ ዘንድ ታገኙአቸዋላችሁ፤ በወደዳችሁም
ጊዜ መልካም ታደርጉላቸዋላችሁ፤ እኔን ግን
ዘወትር የምታገኙኝ አይደለም። ፰ይህቺም ያላ
ትን አደረገች፤ አስቀድማም ለቀብሬ ሥጋዬን
ቀባች። ፱እውነት እላችኋለሁ፤ ይህን ወንጌል
በሚሰብኩበት በዓለሙ ሁሉ ይህች ሴት ያደረ
ገችውን ይናገሩላታል፤ ያስቡአታልም።"

### አስቆሮታዊው ይሁዳ አሳልፎ እንደ ሰጠው
(ማቴ. ፳፮፥፲፬-፲፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፫-፮)

፲ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ ያስቆሮቱ ሰው ይሁ
ዳም ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጣቸው ዘንድ ወደ
ካህናት አለቆች ሄደ። ፲፩ሰምተውም ደስ አላቸ
ውና ሣላሳ ብር ሊሰጡት ተዋዋሉት፤ በስው
ርም አሳልፎ ሊሰጣቸው ይሻ ነበር።

### ስለ ፋሲካ በዓል
(ማቴ. ፳፮፥፲፯-፳፭፤ ሉቃ. ፳፪፥፯-፲፬)

፲፪የፋሲካዉንም በግ በሚያርዱበት በመጀ
መሪያው የቂጣ በዓል ቀን ደቀ መዛሙርቱ፥
"ፋሲካን ትበላ ዘንድ፥ ወዴት ሄደን ልናዘጋ
ጅልህ ትወዳለህ?" አሉት። ፲፫ከደቀ መዛሙር
ቱም ሁለቱን ላካቸው፤ እንዲህም አላቸው፥
"በፊታችሁ ወደ አለችው ከተማ ሂዱ፤ የውኃ
ማድጋ የተሸከመ ሰውም ታገኛላችሁ፤ እርሱ
ንም ተከተሉት። ፲፬ወደ ገባበትም ቤት ገብታ
ችሁ፥ ባለቤቱን፦ መምህር ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር ፋሲካን የምበላበት አዳራሽ ወዴት ነው?
ብሎሃል በሉት። ፲፭እርሱም የተነጠፈና የተዘ
ጋጀ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤ በዚያ አዘ
ጋጁልን።" ፲፮ደቀ መዛሙርቱም ወደ ከተማ
ሄዱ፤ እንዳላቸውም አገኙና ፋሲካን አዘጋጁ።
፲፯በመሸም ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙ
ርቱ ጋር ሄደ።

፲፰በማዕድም ላይ ተቀምጠው ሲበሉ ጌታችን
ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፥ "እውነት እላችኋ
ለሁ፤ ከእናንተ አንዱ እርሱም ከእኔ ጋር የሚ
በላው ያሲዘኛል።" ፲፱እያንዳንዳቸውም፥ "ከቶ
እኔ እሆን?" እያሉ ይተክዙ ጀመር። ፳እርሱም
መልሶ እንዲህ አላቸው፥ "ከዐሥራ ሁለታችሁ
አንዱ ከእኔ ጋር እጁን ወደ ወጭቱ የሚያጠ
ልቀው ነው። ፳፩የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ
ተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን፥ የሰው ልጅ በእጁ
ለሚሰጥ ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወ
ለደ በተሻለው ነበር።"

### ስለ ሥጋዉና ስለ ደሙ ሥርዐት
(ማቴ. ፳፮፥፳፮-፴፤ ፩ቆሮ. ፲፩፥፳፫-፳፭)

፳፪ሲበሉም ጌታችን ኢየሱስ ኅብስቱን አን
ሥቶ ባርኮ ቈርሶም፥ "ይህ ሥጋዬ ነው፤ እንኩ
ብሉ" ብሎ ሰጣቸው። ፳፫ጽዋዉንም አንሥቶ
አመስግኖ፥ "እንኩ ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ"
ብሎ ሰጣቸው።[፩] ፳፬እንዲህም አላቸው፥ "ስለ
ብዙዎች የሚፈስሰው የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ
ነው። ፳፭እውነት እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር
መንግሥት አዲስ አድርጌ እስከምጠጣባት እስ
ከዚያች ቀን ድረስ እንግዲህ ከዚህ የወይን ፍሬ
ጭማቂ አልጠጣም።" ፳፮የምስጋና መዝሙርም
ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ።

### ስለ ሐዋርያት መበተን
(ማቴ. ፳፮፥፴፩-፴፭፤ ዮሐ. ፲፫፥፴፮-፴፰)

፳፯ጌታችን ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው፥ "በዚች ሌሊት ሁላችሁ ትክ
ዱኛላችሁ፤ 'ጠባቂዉን እገድለዋለሁ፤ በጎቹም
ይበተናሉ' የሚል ጽሑፍ አለና። ፳፰ነገር ግን
ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ።"
፳፱ጴጥሮስም፥ "ሁሉም ቢክዱህ እንኳን እኔ
ከቶ አልክድህም" አለው። ፴ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ "እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ በዚች ሌሊት
ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ አንተ ሦስት ጊዜ
ትክደኛለህ" አለው። ፴፩ጴጥሮስ ግን ቃሉን አበ
ርትቶ፥ "ከአንተ ጋር የምሞት እንኳ ቢሆን
ከቶ አልክድህም" አለ። ሁሉም እንደ እርሱ
አሉ።

### በጌቴሴማኒ ስለ መጸለዩ
(ማቴ. ፳፮፥፴፮-፵፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፴፱-፵፮)

፴፪ጌቴሴማኒ ተብላ ወደምትጠራ የአትክልት
ቦታም ሄዱ፤ ደቀ መዛሙርቱንም፥ "ወደዚያ
ሄጄ እስክጸልይ ድረስ በዚህ ተቀመጡ" አላ
ቸው። ፴፫ጴጥሮስን፥ ያዕቆብንና ዮሐንስንም
ከእርሱ ጋር ወሰዳቸው፤ ያዝንና ይተክዝም
ጀመረ። ፴፬እንዲህም አላቸው፥ "ነፍሴ እስከ
ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ተቀመጡ፤

---

[፩] ግሪኩ "ጽዋዉንም አንሥቶ ያዘ አመስግኖም ሰጣቸው፤ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ" ይላል።

፲፬፥፯ ዘዳ. ፲፭፥፲፩። ፲፬፥፲፰ መዝ. ፵፥፱። ፲፬፥፳፬ ዘፀ. ፳፬፥፰፤ ኤር. ፴፩፥፴፩-፴፬። ፲፬፥፳፯ ዘካ. ፲፫፥፯።
፲፬፥፳፰ ማቴ. ፳፰፥፲፮።

እንግዲህም ትጉ።” ፴፭ከዚህም በኋላ፥ ጥቂት
እልፍ ብሎ በምድር ላይ ሰገደ፤ ይቻል እንደ
ሆነም ያቺ ሰዓት ከእርሱ ታልፍ ዘንድ ጸለየ።
፴፮“አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህቺን
ጽዋ ከእኔ አሳልፋት፤ ነገር ግን የአንተ ፈቃድ
ይሁን፤ የእኔ ፈቃድም አይደለም።” ፴፯በተመ
ለሰ ጊዜም ተኝተው አገኛቸው፤ ጴጥሮስንም
እንዲህ አለው፥ “ስምዖን ሆይ፥ ተኝተሃልን?
አንዲት ሰዓት እንኳ መትጋት አትችልምን?
፴፰ወደ ፈተናም እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ፤
መንፈስ ይሻልና፥ ሥጋ ግን ይደክማልና።”
፴፱ዳግመኛም ሄዶ ጸለየ፤ ያንኑ ቃል ብቻም
ተናገረ። ፵ዳግመኛም በተመለሰ ጊዜ ተኝተው
አገኛቸው፤ ዐይኖቻቸው በእንቅልፍ ፈዝዘው ነበ
ርና፤ የሚናገሩትንም አያውቁም ነበርና። ፵፩በሦ
ስተኛውም መጥቶ እንዲህ አላቸው፥ “እንግዲ
ህስ ተኙ፥ ዕረፉም፤ አሁን ጊዜዉ ደርሶአልና፤
እነሆ፥ የሰውን ልጅ በኃጥአን እጅ አሳልፈው
ይሰጡታል። ፵፪ተነሡ እንሂድ፤ እነሆ፥ የሚያ
ሲዘኝ መጥቶአል።”

## ለአይሁድ ተላልፎ ስለ መሰጠቱ

(ማቴ. ፳፮፥፵፯-፶፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፵፯-፶፫)

፵፫ሲነጋገራቸውም ወዲያውኑ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ያስቆሮቱ ሰው ይሁዳ መጣ፤ ከእርሱም
ጋር ከካህናት አለቆች፥ ከጸሓፊዎችና ከሽማግ
ሎችም የተላኩ፥ ሾተልና ጎመድ የያዙ ብዙ
ሰዎች ነበሩ። ፵፬የሚያሲዘውም ምልክት ሰጣ
ቸው፥ “የምስመው እርሱ ነውና ያዙት፤ ተጠ
ንቅቃችሁም ውሰዱት” አላቸው። ፵፭ያንጊ
ዜም ወደእርሱ መጣና፥ “መምህር ሆይ፥”
ብሎ ሳመው። ፵፮በእርሱም ላይ እጃቸውን ዘር
ግተው ያዙት። ፵፯ከእርሱ ጋር ቆመው ከነበ
ሩትም አንዱ ሰይፉን መዝዞ የሊቀ ካህናቱን
አገልጋይ መታው፤ ጆሮውንም ቈረጠው።
፵፰ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥
“እንደ ሌባ ተከታትላችሁ በሾተልና በጎመድ
ልትይዙኝ መጣችሁን? ፵፱በመቅደስም ሳስተ
ምር ዘወትር ከእናንተ ጋር ስኖር፥ አልያዛችሁ
ኝም፤ ነገር ግን በመጻሕፍት ያለው ይፈጸም
ዘንድ ይህ ሆነ።” ፶ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ
ትተውት ሸሹ።

፶፩ዕርቃኑን በነጠላ የሸፈነ አንድ ጐልማሳም
ይከተለው ነበር፤ ጐልማሶችም ያዙት። ፶፪እርሱ
ግን ነጠላዉን ትቶ ዕራቁቱን ሸሸ።

## በአደባባይ ስለ መቆሙ

(ማቴ. ፳፮፥፶፯-፷፰፤ ሉቃ. ፳፪፥፶፬፡፶፭)

፶፫ጌታችን ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰ
ዱት፤ የካህናት አለቆች፥ ጸሓፊዎችና ሽማ
ግሎችም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። ፶፬ጴጥሮስም
እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ ድረስ ከሩቁ
ተከተለው፤ በብርሃኑ በኩልም ከሎሌዎች ጋር
ተቀምጦ እሳት ይሞቅ ነበር። ፶፭የካህናት አለ
ቆችና ሸንጎዎች ሁሉ ይገድሉት ዘንድ ጌታ
ችን ኢየሱስን ይከስሱት ዘንድ የሐሰት ምስ
ክሮችን ፈለጉ፤ ነገር ግን አጡ። ፶፮በሐሰትም
የመሰከሩበት ብዙዎች ነበሩ፤ ነገር ግን ቃላ
ቸው አንድ አልሆነም። ፶፯ተነሥተውም በሐ
ሰት የተናገሩ የሐሰት ምስክሮች ነበሩ። ፶፰“እኔ
ይህን የሰው እጅ የሠራውን ቤተ መቅደስ አፍ
ርሼ፥ በሦስተኛው ቀን የሰው እጅ ያልሠራው
ሌላ ቤተ መቅደስ እሠራለሁ ሲል እኛ ሰምተ
ነዋል” አሉ። ፶፱ከዚህም ጋር ምስክርነታቸው
አንድ አልሆነም። ፷ሊቀ ካህናቱም በመካከላ
ቸው ተነሥቶ፥ “እነዚህ ይህን ያህል ሲመ
ሰክሩብህ የምትመልሰው አንዳች የለህምን?”
ብሎ ጌታችን ኢየሱስን ጠየቀው። ፷፩እርሱ ግን
ዝም አለ፥ ምንም አልመለሰለትም፤ ሊቀ ካህና
ቱም ዳግመኛ መረመረው፤ “የቡሩክ ልጅ ክር
ስቶስ አንተ ነህን?” አለው። ፷፪ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ “አዎን፥ እኔ ነኝ፤ የሰውን ልጅ በኀ
ይል ቀኝ ተቀምጦ፤ በሰማይ ደመና ሲመጣ
ታዩታላችሁ” አለው። ፷፫ሊቀ ካህናቱም ልብ
ሱን ቀድዶ እንዲህ አለ፥ “እንግዲህ ምን ምስ
ክር ትሹለታላችሁ? ፷፬እነሆ፥ እናንተ ራሳችሁ
ስድቡን ሰማችሁ፤ እንግዲህ ምን ትላላችሁ?”
ሁሉም፥ “ሞት ይገባዋል” ብለው ፈረዱበት።
፷፭ከመካከላቸውም አንዳንዶች ይተፉበት ነበር፤
ፊቱንም ሸፍነው ራሱን ይመቱትና፤ “ክርስ
ቶስ፥ ትንቢት ተናገር” ይሉት ነበር፤ ሎሌዎ
ችም መላልሰው በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።

## ስለ ጴጥሮስ ክሕደት

(ማቴ. ፳፮፥፷፱-፸፭፤ ዮሐ. ፲፰፥፲፭-፲፰)

፷፮ጴጥሮስም በግቢው ውስጥ በታች ቤት
ሳለ፥ ከሊቀ ካህናቱ ገረዶች አንዲት ብላቴና
መጣች። ፷፯ጴጥሮስንም እሳት ሲሞቅ አየችው፤
አስተውላም፥ “አንተ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር
ነበርህ” አለችው። ፷፰እርሱ ግን “የምትዪውን

---

፲፬፥፵፱ ሉቃ. ፲፱፥፵፯፤ ፳፩፥፴፯። ፲፬፥፶፰ ዮሐ. ፪፥፲፱። ፲፬፥፷፪ ዳን. ፯፥፲፫። ፲፬፥፷፬ ዘሌ. ፳፬፥፲፮።

አላውቅም፤ ልብም አላደርገውም" ብሎ ካደ፤
ከቅፅሩም ወደ ውጭ ወደ ደጅ ወጣ፤ ዶሮም
ጮኸ። ፷፱ ደግመኛም ሴላዪቱ ብላቴና አየች
ውና ከዚያ ቆመው ለነበሩት፥ "ይህም ከእነ
ርሱ ወገን ነው" አለቻቸው፤ እርሱም ሁለተኛ
ካደ። ፸ ከጥቂት ጊዜም በኋላ ከዚያ ቆመው የነ
በሩት ጴጥሮስን፥ "በእውነት አንተ ከእነርሱ
ወገን ነህ፤ አንተ ገሊላዊ ነህና፤ አነጋገርህም
ያስታውቅብሃል" አሉት። ፸፩ እርሱ ግን "ይህን
የምትሉትን ሰው አላውቀውም" እያለ ይም
ልና ይረገም ጀመር፤ ያንጊዜም ዶሮ ሁለተኛ
ጮኸ። ፸፪ ጴጥሮስም "ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይ
ጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" ያለውን፤ የጌታ
ችን የኢየሱስን ቃል ዐስቦ አለቀሰ።

## ምዕራፍ ፲፭

### በጲላጦስ ፊት ስለመቆሙ

(ማቴ. ፳፯፥፩-፪፤ ሉቃ. ፳፫፥፩-፭)

፩ በነጋ ጊዜም የካህናት አለቆች፥ ሽማግሌዎ
ችና ጸሐፊዎች ሸንጎውም ሁሉ ተማከሩ፤ ጌታ
ችን ኢየሱስንም አስረው ወስደው ለጲላጦስ
ሰጡት። ፪ ጲላጦስም፥ "የአይሁድ ንጉሥ አንተ
ነህን?" ብሎ ጠየቀው፤ ጌታችን ኢየሱስም፥
"አንተ ትላለህ" አለው። ፫ የካህናት አለቆችም
በብዙ ነገር ከሰሱት፤ እርሱ ግን የመለሰው
ነገር የለም። ፬ ጲላጦስም፥ "ይህን ያህል ሲከ
ስሱህ አንዳች አትመልስምን?" ብሎ እንደገና
ጠየቀው። ፭ ጌታችን ኢየሱስ ግን ጲላጦስ እስኪ
ያደንቀው ድረስ ምንም አልመለሰለትም።

፮ በየበዓሉም ከእስረኞች የመረጡትን አንዱን
ይፈታላቸው ነበር። ፯ ከክፉ አድራጊዎችና ከነ
ፍሰ ገዳዮች ጋር የታሰረ ስሙ በርባን የሚባል
አንድ ሰው ነበር። ፰ ሕዝቡም ወጥተው እንደ
አስለመደ ያደርግላቸው ዘንድ እየጮኹ ለመኑ።
፱ ጲላጦስም መልሶ፥ "የአይሁድን ንጉሥ እፈ
ታላችሁ ዘንድ ትወዳላችሁን?" አላቸው። ፲ የካ
ህናት አለቆች በቅናት አሳልፈው እንደ ሰጡት
ያውቅ ነበርና። ፲፩ የካህናት አለቆች ግን በርባ
ንን እንዲፈታላቸው ይለምኑት ዘንድ ሕዝቡን
አነሣሡአቸው። ፲፪ ጲላጦስም መልሶ፥ "እንግ
ዲህ የአይሁድ ንጉሥ የተባለውን ምን ላደር
ገው ትወዳላችሁ?" አላቸው። ፲፫ እነርሱም እን
ደገና፥ "ስቀለው" እያሉ ጮኹ። ፲፬ ጲላጦስም፥
"ምን ክፉ ሥራ ሠራ?" አላቸው፤ እነርሱ
ግን፥ "ስቀለው" እያሉ አብዝተው ጮኹ።
፲፭ ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ ሊያደርግ ወድዶ
በርባንን ፈታላቸው፤ ጌታችን ኢየሱስንም
ገርፎ ሊሰቅሉት ሰጣቸው።

### ጭፍሮች በእርሱ ላይ ስለ መዘባበታቸው

(ማቴ. ፳፯፥፳፯-፴፩፤ ዮሐ. ፲፱፥፪-፫)

፲፮ ወታደሮችም ወደ ግቢ ውስጥ ወደ ፍርድ
ሸንጎ አገቡት፤ ባለወጎቹንም ጭፍሮች ሁሉ
ጠሩ። ፲፯ ቀይ ሐርም አለበሱት፤ የእሾህ አክ
ሊልም ጐንጉነው ደፉበት፤ ተዘባበቱበትም።
፲፰ "የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ
ይሁን" አሉት። ፲፱ ራሱንም በዘንግ ይመቱትና
ይተፉበት፥ ተንበርክከውም በፊቱ ይሰግዱለት
ነበር። ፳ ከተዘባበቱበትም በኋላ ያን ቀይ ሐር
ገፈፉት፤ ልብሱንም አልብሰው ወደሚሰቅሉ
በት ቦታ ወሰዱት።

፳፩ ስምዖን ቀሬናዊ የተባለ አንድ መንገድ
አላፊ እርሱም የእስክንድሮስና የሩፎስ አባት
ከዱር ሲመጣ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስ
ገደዱት። ፳፪ በትርጓሜው የራስ ቅል ወደሚ
ሉት ቦታ ጎልጎታ ወደሚባል ስፍራ ወሰዱት።
፳፫ ከከርቤም ጋር የተቀላቀለ ወይን እንዲጠጣ
ሰጡት፤ እርሱ ግን አልጠጣም አለ።

### ስለ ስቅለቱ

(ማቴ. ፳፯፥፴፪-፵፬፤ ሉቃ. ፳፫፥፳፮-፵፫)

፳፬ ሰቀሉትም፤ በልብሱም ላይ ዕጣ ተጣ
ጥለው እንደ ድርሻቸው ተካፈሉ። ፳፭ ሲሰቅ
ሉትም ሦስት ሰዓት ነበር። ፳፮ የበደሉ ደብዳ
ቤም "የአይሁድ ንጉሥ ነው" ይል ነበር።
፳፯ ከእርሱ ጋርም ሁለት ወንበዴዎችን አንዱን
በቀኙ፥ አንዱንም በግራዉ ሰቀሉ። ፳፰ መጽሐ
ፍም፥ "ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ" ያለው
ተፈጸመ። ፳፱ መንገድ ተላላፊዎችም ይሰድቡት
ነበር፤ ራሳቸውንም እየነቀነቁ እንዲህ ይሉት
ነበር፥ "ቤተ መቅደስን የምታፈርሰው፥ በሦ
ስት ቀንም የምትሠራው ሆይ፥ ፴ ከመስቀል
ወርደህ ራስህን አድን፤" ፴፩ እንዲሁ የካህናት
አለቆችና ጸሐፊዎችም እየዘበቱበት "ሌላውን
የሚያድን፥ ራሱን ማዳን የማይችል" ይሉት
ነበር። ፴፪ "እርሱ የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስ
ከሆነ እስኪ አሁን ከመስቀሉ ይውረድና አይ

---

፲፭፥፳፩ ሮም ፲፮፥፲፫። ፲፭፥፳፬ መዝ. ፳፩፥፲፰። ፲፭፥፳፰ ኢሳ. ፶፫፥፲፪።
፲፭፥፳፱ መዝ. ፳፩፥፯፤ ፻፰፥፳፭፤ ማር. ፲፬፥፶፰፤ ዮሐ. ፪፥፲፱።

ተን እንመንበት፤” አሉ፤ አብረውት የተሰቀሉ
ትም ያሽሙአጥጡት ነበር።

### በመስቀል ላይ ስለ መሞቱ

(ማቴ. ፳፯፥፵፭-፶፮፤ ዮሐ. ፲፱፥፳፰-፴)

፴፫ቀትርም በሆነ ጊዜ ፀሐይ ጨለመ፤ ምድ
ርም ሁሉ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጨለማ
ሆነ። ፴፬ዘጠኝ ሰዓትም በሆነ ጊዜ ጌታችን ኢየ
ሱስ በታላቅ ቃል፥ “ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበ
ቅታኒ?” ብሎ ጮኸ፤ ትርጓሜውም “አም
ላኬ አምላኪ ለምን ተውኸኝ?” ማለት ነው።
፴፭በዚያ ቆመው ከነበሩትም፥ “ኤልያስን ይጠ
ራል” አሉ። ፴፮አንዱም ሮጦና ሰፍነጉን መጻጻ
መልቶ በዘንግ አስሮ አጠጣውና፥ “ዝም በሉ፤
ኤልያስ መጥቶ ያወርደው እንደ ሆነ እንይ”
አለ። ፴፯ጌታችን ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ
ጮኸ፤ ነፍሱንም ከሥጋው ለየ። ፴፰የቤተ መቅ
ደሱ መጋረጃም ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀ
ደደ። ፴፱ፊት ለፊት የቆመው የመቶ አለቃም
እንዲህ ጮኾ እንደ ሞተ ባየ ጊዜ፥ “ይህ ሰው
በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነው” አለ።
፵ከሩቅም ቆመው የሚያዩት ሴቶች ነበሩ፤
እነርሱም ማርያም መግደላዊት፥ የታናሹ ያዕ
ቆብ እና የዮሳ እናት ማርያም፥ ሰሎሜም
ነበሩ። ፵፩እነዚህም ከገሊላ ጀምሮ ይከተሉትና
ያገለግሉት የነበሩ ናቸው፤ ሌሎችም ብዙዎች
ከእርሱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የወጡ ነበሩ።

### ወደ መቃብር ስለመውረዱ

(ማቴ. ፳፯፥፶፯-፷፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፶-፶፮)

፵፪ያንጊዜም ዐርብ ሲመሽ የሰንበት መግቢያ
ነበር። ፵፫ደግና ምክር ዐዋቂ የነበረ ሰው፥ እር
ሱም የእግዚአብሔርን መንግሥት ተስፋ ያደ
ርግ የነበረ የአርማትያሱ ዮሴፍ መጣ፤ ደፍሮም
ወደ ጲላጦስ ገባና የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ
ለመነ። ፵፬ጲላጦስም፡- እንዴት እንደ ሞተ አደ
ነቀ፤ ወታደሩንም ጠርቶ፥ “ፈጽሞ ሞተን?”
አለው፤ ወታደሩም፥ “አዎን፥ ሞተ” አለው።[፩]
፵፭እንደ ሞተም ከወታደሩ ተረድቶ ሥጋዉን
ለዮሴፍ እንዲሰጡት አዘዘ። ፵፮ዮሴፍም በፍታ
ገዛ፤ አውርዶም በበፍታ ገንዞ ከዐለት ባስፈለ
ፈለው አዲስ መቃብር ቀበረው፤ ድንጋይም
አገላብጦ የመቃብሩን አፍ ገጠመ። ፵፯ማርያም
መግደላዊትና የዮሳ እናት ማርያምም የቀበሩ
በትን አዩ።

## ምዕራፍ ፲፮

### ከሙታን ተለይቶ ስለመነሣቱ

(ማቴ. ፳፰፥፩-፰፤ ሉቃ. ፳፬፥፩-፲፪)

፩ሰንበትም ባለፈች ጊዜ ማርያም መግደላ
ዊት፥ የያዕቆብ እናት ማርያም፥ ሰሎሜም መጥ
ተው ሥጋዉን ሊቀቡ ሽቱ ገዙ። ፪በእሑድ ሰን
በትም እጅግ ማልደው ፀሐይ በወጣ ጊዜ፥ ወደ
መቃብር ሄዱ። ፫እርስ በርሳቸውም፥ “ድንጋ
ዩቱን ከመቃብሩ አፍ ላይ ማን ያነሣልናል?”
አሉ፤ ድንጋዩቱ እጅግ ታላቅ ነበረችና። ፬አሻ
ቅበውም በተመለከቱ ጊዜ ደንጋዩቱ ተንከባ
ልላ አዩ። ፭ወደ መቃብሩም በገቡ ጊዜ አንድ
ጐልማሳ ነጭ ልብስ ለብሶ በስተቀኝ ተቀምጦ
አገኙና ደነገጡ። ፮እርሱም እንዲህ አላቸው፥
“አትደንግጡ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱ
ስን ትሻላችሁን? ተነሥቶአል፤ በዚህስ የለም፤
የተቀበረበትም ቦታ እነሆ። ፯ነገር ግን፥ ሂዱና
ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስም ወደ ገሊላ እን
ደሚቀድማቸው ንገሩአቸው፤ እንደ ነገራቸውም
በዚያ ያዩታል።” ፰ከመቃብርም ወጥተው
ሸሹ፤ ፍርሀትና ድንጋጤ ይዞአቸዋልና፤ ስለ
ፈሩም ለማንም አልተናገሩም፤ ያዘዛቸውንም
ሁሉ ለጴጥሮስና ለወንድሞቹ ተናገሩ። ጌታችን
ኢየሱስም ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ተገ
ለጠላቸውና፥ ለዘለዓለም ሕይወት የሚሆን የማ
ይለወጥ ቅዱስ ወንጌልን ለፍጥረቱ ሁሉ ከምሥ
ራቅ እስከ ምዕራብ ይሰብኩ ዘንድ ላካቸው።
፱በእሑድ ሰንበትም ማለዳ ተነሥቶ ሰባት
አጋንንትን ላወጣላት ለማርያም መግደላዊት
አስቀድሞ ታያት።

### ለብዙዎች ስለመታየቱ

(ማቴ. ፳፰፥፱-፲፤ ዮሐ. ፳፥፲፩-፲፰)

፲እርስዋም ሄዳ ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሲያዝ
ኑና ሲያለቅሱ ሳሉ ነገረቻቸው። ፲፩እነርሱ ግን
ሕያው እንደ ሆነ፥ ለእርስዋም እንደ ተገለጠ
ላት በሰሙ ጊዜ አላመንዋትም።
፲፪ከዚህም በኋላ፥ ከእነርሱ ለሁለቱ ወደ
ገጠር ሲሄዱ በሌላ መልክ ተገለጠላቸው። ፲፫እነ

---

፩ “ወታደሩም አዎን ሞተ አለው” የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፭፥፴፬ መዝ. ፳፩፥፩። ፲፭፥፴፮ መዝ. ፷፰፥፳፩። ፲፭፥፴፰ ዘፀ. ፳፮፥፴፩-፴፫። ፲፭፥፵፩ ሉቃ. ፰፥፪-፫።
፲፮፥፯ ማቴ. ፳፮፥፴፪፤ ማር. ፲፬፥፳፰።

ርሱም ደግሞ ሄደው ለባልንጀሮቻቸው ነገሩ፤
እነርሱንም ቢሆን አላመኑአቸውም። ፲፬ከዚህም
በኋላ፥ ደግሞ ዐሥራ አንዱ በማዕድ ተቀም
ጠው ሳለ ተገለጠላቸው፤ እንደ ተነሣ ያዩትን
አላመኑአቸውምና ስለ ሃይማኖታቸው ጉድለት
ገሠጻቸው፤ የልባቸውንም ጽናት ነቀፈ።

### ሐዋርያትን ስለ መሾሙ

(ማቴ. ፳፰፥፲፮-፳፤ ሉቃ. ፳፬፥፴፮-፵፱)

፲፭እንዲህም አላቸው፥ "ወደ ዓለም ሁሉ
ሂዱ፤ ለፍጥረትም ሁሉ ወንጌልን ስበኩ።
፲፮ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን
ይፈረድበታል። ፲፯ይህችም ምልክት በስሜ
የሚያምኑትን ትከተላቸዋለች፤ በስሜ አጋን
ንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ።
፲፰እባቦችንም በእጃቸው ይይዛሉ፤ የሚጐዳቸ
ውም ነገር የለም፤ የሚገድል መርዝ ቢጠጡም
የሚጐዳቸው የለም፤ በድውያን ላይም እጃቸ
ውን ይጭናሉ፤ ድውያኑም ይፈወሳሉ።"

### ወደ ሰማይ ስለማረጉ

(ሉቃ. ፳፬፥፶-፶፫፤ ሐ.ሥ. ፩፥፱-፲፩)

፲፱ጌታችን ኢየሱስም ከተነጋገራቸው በኋላ
ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም[፩] በእግዚአብሔር
ቀኝ ተቀመጠ። ፳እነርሱም ወጥተው ጌታ እየረ
ዳቸው፥ ቃሉንም በማያቋርጥ ተአምር እያጸና
ላቸው በስፍራው ሁሉ አስተማሩ።

ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ወንጌላዊው
ማርቆስ የጻፈው ወንጌል ተፈጸመ፤ የጻፈ
ውም በሮም ሀገር በሮማይስጥ ቋንቋ፤ ጌታ
ችን በሥጋ ወደ ሰማይ ባረገ በዐሥራ አንድ
ዓመት፥ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በአራት
ዓመት ነው።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

---

፩ "በአባቱም" የሚለው በግሪኩ የለም።

፲፮፥፲፭ ሐሥ. ፩፥፰።    ፲፮፥፲፱ ሐ.ሥ. ፩፥፱-፲፩።

ይሰርቁት ለሕዝቡም ከሙታን ተለይቶ ተነሣ
እንዳይሉ፥ እስከ ሦስት ቀን መቃብሩ እንዲ
ጠበቅ እዘዝ፤ የኋለኛዪቱ በደሉ ከፊተኛዪቱ
የምትከፋ ትሆናለችና።” ፷፭ ጲላጦስም፥ “ጠባ
ቆች አሏችሁ፤ [፪] ሄዳችሁም እንደምታውቁ አስ
ጠብቁ” አላቸው። ፷፮ እነርሱም ሄደው ከጠባ
ቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስ
ጠበቁ።

## ምዕራፍ ፳፰

### ጌታችን ስለ መነሣቱ

፩ በሰንበትም ማታ ለእሑድ አጥቢያ ማር
ያም መግደላዊትና ሁለተኛዋ ማርያም መቃ
ብሩን ሊያዩ መጡ። ፪ እነሆ፥ ታላቅ የምድር
መናወጥ ሆነ፤ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰ
ማይ ወርዶአልና፤ ቀርቦም በመቃብሩ አፍ
ላይ ድንጋይዋን አንከባሎ በላይዋ ተቀመጠ።
፫ መልኩም እንደ መብረቅ፥ ልብሱም እንደ
በረዶ ነጭ ነበረ። ፬ እርሱንም ከመፍራት የተ
ነሣ መቃብሩን የሚጠብቁ ታወኩ፤ እንደ በድ
ንም ሆኑ። ፭ መልአኩም መልሶ ሴቶችን እን
ዲህ አላቸው፤ “እናንተስ አትፍሩ፤ የተሰ
ቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና።
፮ በዚህ የለም፤ እርሱ እንደ ተናገረው ተነ
ሥቶአል፤ ነገር ግን ኑና ተቀብሮበት የነበረ
ውን ቦታ እዩ። ፯ ፈጥናችሁም ሂዱና፡- ከሙ
ታን ተለይቶ ተነሣ፤ እነሆ፥ ወደ ገሊላ ይቀ
ድማችኋል፤ በዚያም ታዩታላችሁ፤ ብላችሁ
ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው፤ እነሆም፥ ነገር
ኋችሁ።” ፰ በፍርሀትና በታላቅ ደስታም ከመ
ቃብሩ ፈጥነው ሄዱ፤ ለደቀ መዛሙርቱም
ይነግሩአቸው ዘንድ ሮጡ። ፱ እነሆም፥ ጌታ
ችን ኢየሱስ አገኛቸውና፥ “ሰላም ለእናንተ
ይሁን” አላቸው፤ እነርሱም ቀርበው እግሩን
ይዘው ሰገዱለት። ፲ ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየ
ሱስ እንዲህ አላቸው፥ “አትፍሩ ሂዱና ወደ
ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሩአቸው፤ በዚ
ያም ያዩኛል።”
፲፩ እነርሱም ከሄዱ በኋላ ጠባቆች ወደ ከተማ
ገብተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች ነገሩ።
፲፪ ተሰብስበውም ከሽማግሌዎች ጋር መክረው
ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጡአቸው። ፲፫ እንዲ
ህም አሏቸው፥ “ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙ
ርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ። ፲፬ ይህም
ነገር በገገሮው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ እኛ እና
ሳምነዋለን፤ እናንተንም ያለ ሥጋት እንድትኖሩ
እናደርጋለን።” ፲፭ ጭፍሮችም ገንዘቡን ተቀብ
ለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ፤ ይህም
ነገር እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁድ ዘንድ ሲነ
ገር ይኖራል።
፲፮ ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ጌታ
ችን ኢየሱስ ወደ አዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ
ሄዱ። ፲፯ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ እኩሌቶቹ [፩]
ግን ተጠራጠሩ። ፲፰ ጌታችን ኢየሱስም ቀርቦ፡-
እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ “ሥልጣን ሁሉ
በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። ፲፱ እንግዲህ ሂዱና
በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመ
ቃችኋቸው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ። ፳ ያዘዝኋ
ችሁንም እንዲጠብቁ አስተምሩአቸው፤ እኔም
እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር
እኖራለሁ።”

ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሐዋርያ ማቴዎስ በምድረ ፍልስጥኤም በዕብራይስጥ ቋንቋ የጻፈው ወንጌል ተፈጸመ፤ መንፈስ ቅዱስ እያተጋው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በስምንተኛው ዓመት፤ ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያዉ ዓመት ጻፈው።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

፪ ግእዙ “ንሥኡ ሰገራተ ...” ይላል።
፩ ግሪኩ “... አንዳንዶቹ ግን ...” ይላል።
፳፰፥፩-፲፫ ማር. ፲፮፥፩-፲፤ ሉቃ. ፳፬፥፩-፲፪፤ ዮሐ. ፳፥፩-፲። ፳፰፥፲፮ ማቴ. ፳፮፥፴፪፤ ማር. ፲፬፥፳፰።
፳፰፥፲፱ ሐ.ሥ. ፩፥፰።